# ጤናችን

ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን /March 8/ ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀ ልዩ ዕትም የካቲት 29/2009

## የሴቶች የቁጠባ ባሕል ማደግ ለተሻለ የጤና አገልግሎት!




የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴምክራሳዊ ረፐብሊክ መንግስት
የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት



# እንኳን አደረሳችሁ!

የሴቶች የቁጠባ ባህል ማደግ ለሕዳሴያችን መሰረት ነዉ!

41ኛዉ ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን /March 8/

በፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት
በአመት አንድ ጊዜ እየተዘጋጀ የሚሰራጭ መፅሄት፡፡

## ማውጫ


- ማውጫ........ I
- የክቡር ሚኒስቴሩ መልዕክት........ 1
- የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር መልዕክት........ 2
- የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ከየት ወዴት? ........ 3
  - የስርዓተ ጾታ ጉዳይን ተቋማዊ ለማድረግ የተተገበሩ ጉልህ ስራዎች........
  - ሴቶች ወደ አመራርነት ከማምጣት ጋር ተያይዘው የተከናወኑ ክንውኖች........
  - ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ በመስራት ረገድ ያለ ተሞክሮ........
- የሴቶችን ሁለንተናዊ ጤና ከማበልፀግ ጋር ተያይዞ መረጃዎች ምን ይላሉ ........ 4
- የክፍሉ የስራ እንቅስቃሴ በሌሎች ዕይታ ........ 5
- አዝናኝ ቁመነገር አዘል ወጎች እዉነታዎችና አባባሎች ........ 6
- ተንከባካቢ፣ ተገልጋይን አክባሪና ርህሩህነት የተሞላበት  የጤና አገልግሎት ........ 7
- የሴት ልጅ ግርዛትና ጤና........ .
- ዜና........ 8
- ካነበብነዉ ........ 9
- የጤና ኤክስቴንሽን መርሃ-ግብሩ ሴቶችን ተጠቃሚ በማድረግ ረገድ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎችአሉት!"........ 10
- የእናቶችን ሞት ለመቀነስ አሁንም ብዙ መሰራት አለበት... ብዙ የታቀዱ ስራዎችም አሉ!..... 11
- በጤናው ዘርፍ ሴቶችን ወደ ውሳኔ ሰጭነት ሚና ለማምጣት ብዙ መሰራት አለበት!........
- ተግባራትን በምስል........ 12




## የክቡር ሚኒስቴሩ መልዕክት



**ፕሮፌሰር ይፍሩ ብርኃን**
**የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚንስትር**

## በቅድሚያ እንኳን በሃገራችን ለ41ኛ ጊዜ ለሚከበረው አለም አቀፍ የሴቶች ቀን እንኳን አደረሳችሁ! አደረሰን!!

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሃገራችን ህዝቦች ሁለንተናዊ ጤናቸው ተጠብቆ በሃገር ልማት ላይ ተሳታፊና የልማቱም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል ዘርፈ ብዙ ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በተለይም የእናቶችና ህፃናት ጤና ለማሻሻል ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት መከላከልን መሰረት ያደረገና ተደራሽ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ስርአት በማስፈን የእናቶችን ሞት በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ ተችሏል፡፡ ለዚህ ጥረት ስኬት ምክንያት ከሆኑት ዋነኛ ምክንያቶች ውስጥ ፍትሃዊ የጤና አገልግሎ ተደራሽነት መጠናከር፣በጤና ተቋማት የሚሰጡ የእናቶች ጤና አገልግሎቶች ጥራት መሻሻልና አጠቃላይ ማህበረሰቡን ያሳተፉ ንቅናቄዎች መደረጋቸው ተጠቃሽ ናቸው፡፡

የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማሳደግ እየተወሰዱ ካሉ እርምጃዎች አንዱና ዋነኛው የጤና ኤክስቴንሽን መርሃ-ግብር ነው፡፡ ይህ መርሃ-ግብር ሴቶች የነበረባቸውን የጤና አገልግሎትና መረጃ ተደራሽነት ለማጥበብ አይነተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ ሴቶች በስርአተ ፆታ ሚናቸው ምክንያት አብዛኛውን ጊዜ በቤት ውስጥ ስራ ተጠምደው ስለሚውሉ ወደ ጤና ተቋማት በመሄድ አገልግሎት ለማግኘት ጊዜ አያገኙም ነበር፡፡ ይሁንና ይህንን ችግር ለመቅረፍ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ከቤት ወደ ቤት በመሄድና ወደ ማህበረሰቡ ዘልቀው በመግባት ሴቶችን ፊት ለፊት እያገኙ እንዲያስተምሩና አገልግሎት እንዲሰጡ እንዲሁም ከሴቶች የልማት ቡድኖች ጋር በቅርበት እንዲሰሩ መደረጉ ለተገኘው ውጤት ትልቅ አስታዋፅኦ አበርክቷል፡፡ በሌላ በኩል በማህበረሰብ ደረጃ ከሚደረጉ የግንዛቤ ማስጨበጥና የንቅናቄ መድረኮች በተጓዳኝ እናቶች ወደ ጤና ተቋም ሲመጡ የሚያገኙት አገልግሎት ጥራቱ የተጠበቀና ፍላጎቶቻቸውንና ምርጫቸውን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ለማድረግ እየተሰሩ ያሉ ስራዎችም አያሌ ውጤቶችን አስገኝተዋል፡፡ በተለይም የእናቶች በእርግዝና ወቅት የቅድመ ወሊድ ክትትል ፣ በጤና ተቋማት የመውለድ፣ የድህረ ወሊድ ክትትልና የቤተሰብ እቅድ አገልግሎቶች ተጠቃሚነት ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ በማደግ ላይ ይገኛል፡፡ ይህም የእናቶችን ሞት ባለፉት አምስት አመታት ከ ከ100,000 በህይወት ከሚወለዱ ህፃናት ውስጥ በ1990 እ.ኤ.አ 1400 ከነበረው በ2016 ወደ 412/100,000 በዚህም 71% መድረስ ችሏል፡፡

በሌላ አንጻር በጤናው ዘርፍ ተሰማርተው በማገልገል ላይ የሚገኙ ሴት ሰራተኞች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣ ሲሆን በዘርፉ ሴቶችን ወደ አመራርነት ሚና ለማምጣት እየተደረገ ያለው ጥረትም ውጤት እያመጣ ነው፡፡ ምንም እንኳን ልንደርስበት ከምንፈልገው ግብ አንጻር አሁንም ብዙ ስራዎች ቢቀሩም የተመዘገቡ ውጤቶችም አበረታች ናቸው፡፡ ለዚህም ሚኒስቴር መ/ቤታችን የተለያዩ የአቅም ግንባታና ሴቶችን የማብቃት እንዲሁም የአመራር ክህሎት ስልጠናዎችን አጠናክሮ ይቀጥልበታል፡፡

ሁሉም ሰው እንደሚስማማው የሴቶችን ጤና መጠበቅ የቤተሰብን ብሎም የህብረተሰቡን ጤና ለማሻሻል አይነተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡ ከዚህ መነሻነት በጤናው ሴክተር የትራንስፎርሜሽን እቅድ ውስጥ በጉልህ ከተቀመጡ አጀንዳዎች ዋና ዋናዎቹ የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማሳደግ ትኩረት የሚሰጡ ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ የጤና ክብካቤ ጥራትና ፍትሃዊነት ትራንስፎርሜሽንና ርሁሩህ፣ ተገልጋይ አክባሪና ተንከባካቢ የጤና ባለሙያ የመፍጠር እንቅስቃሴዎች ሴቶች ያሉባቸውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ተፅእኖዎች ከግምት ያስገባ አገልግሎትና መረጃ አሰጣጥ ስርአት በማስፈን ለላቀ የሴቶች ተጠቃሚነት ገንቢ ሚና ይኖራቸዋል፡፡ በዚህም መላው የዘርፉ ባለሙያዎች፣ ሰራተኞችና የሚኒስቴር መ/ቤታችን አጋሮች ለላቀ የሴቶች ተጠቃሚነት በምናደርገው ቀጣይ ስራዎች በያሉበት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ከአደራ ጭምር አሳስባለሁ፡፡



*ወ/ሮ ያምሮት አንዱዓለም*
*በፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር*
*የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር*

ሴቶች ሁለንተናዊ ጤናቸው ተጠብቆ በሀገራችን ልማት ውስጥ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል በጤናው ዘርፍ በርካታ ስራዎች በመሰራት ላይ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ስራዎች በአብዛኛው በማህበረሰብ ዉስጥ ያለውን የስርአተ ጾታ አመለካከት ወደ ተሻለ ደረጃ በማሳደግ ሴቶች በማህበረሰቡ የእለት ተእለት ኑሮ ውስጥ ገንቢ ሚና እንዲጫወቱ ከማድረግ አልፎ፤ ማህበረሰቡ ለሴቶች ጤና መሻሻል የበኩሉን አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ሁኔታዎችን አመቻችተዋል፡፡

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እስከ አሁን ድረስ በነበሩት ተከታታይ የጤናዉ ሴክተር ልማት ፕሮግራሞች ዉስጥ ለሴቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ትኩረት በመስጠት በርካታ ስራዎችን ሰርቷል፡፡ እነዚህ በማህበረሰብ ዉስጥ፣ በጤና ተቋማትና በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ላይ የተሰሩ ስራዎች ተስፋ ሰጪ ውጤቶች እንዲመዘገቡ መሰረት ጥለዋል፡፡ በዚህ መልኩ ከተገኙ ዉጤቶች መካከል በእናቶች ቅድመ ወሊድና ድህረ ወሊድ ክትትልና ምርመራ ፣ የእናቶች በጤና ተቋም መዉለድ፣ በቤተሰብ ምጣኔና የስነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ተጠቃሚነት መስኮች  በከተማም ሆነ በገጠር ከፍተኛ መሻሻል የታየባቸው ናቸው፡፡ በዚህም የእናቶችን ሞት በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ተላላፊ ያልሆኑና ከአመጋገብና ንፅህና ጉድለት ጋር ተያይዘዉ በሚከሰቱ የጤና ጠንቆች ዙሪያ የሴቶች ግንዛቤ እንዲያድግና የአስተሳሰብ ለዉጥ እንዲመጣ በተለይ በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የተሰሩ ስራዎች ጉልህ ውጤቶችን አስመዝግበዋል፡፡

ሴቶችና ልጃገረዶች መረጃን በወቅቱና በተገቢ ሁኔታ እንዲያገኙ፣ የስነ ተዋልዶጤና መብቶቻቸዉን እንዲያዉቁና እንዲተገብሩ፣ ከእናቶች ጤና ጋር የተያያዙ መሰረታዊ የቅድመ ወሊድ፣ የወሊድና የድህረ ወሊድ እንዲሁም የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች በነፃ እንዲያገኙ የተሰሩት ስራዎች ለተገኙ ውጤቶች ተጨማሪ ምክንያቶች ናቸው፡፡ ከዚህም በላይ ሴቶች በአንድ ለአምስት ትስስር፣ በሴቶች የልማት ቡድኖችና መሰል አደረጃጀቶች በጤናዉ ስራ ዉስጥ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል፡፡ ይህም በሚሰጣቸዉ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ላይ በመሳተፍ የጤና አገልግሎት ጥራትና ተደራሽነት ላይ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ እድል ፈጥሮላቸዋል፡፡

ዘንድሮ በአለም ለ106ኛ ጊዜና በሃገራችን ለ41ኛ ጊዜ  *"የሴቶች የቁጠባ ባህል ማደግ ለህዳሴያችን መሰረት ነው በሚል ሃገራዊ መሪ ቃልና በሴክተራችን ደግሞ "የሴቶች የቁጠባ ባህል ማደግ ለተሻለ የጤና አገልግሎት"* በሚል መሪ ቃል የሚከበረው  የአለም ሴቶች ቀን ሲከበር በዋነኝነት ሴቶች በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ሌሎች መስኮች ላስመዘገቧቸዉ ድሎች እዉቅና በመስጠት በቀጣይ በሁሉም መስክ ራሳቸውን ለማብቃት የሚያደርጉትን ጥረት ለመደገፍና ለማበረታታት ዝግጁነታችንን እያረጋገጥን መሆን አለበት፡፡

በሌላ በኩል የወጣቶች ጤና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይው ነው፡፡ ለዚህም በአዲሱ የወጣቶች ጤና ስትራቴጂ የተቀመጡት ዝርዝር የማስፈፀሚያ ስልቶች በየደረጃው እንዲተገበሩና የወጣቶች የጤና ሁኔታ እንዲሻሻል በትጋት መስራት ያስፈልጋል፡፡ በየጤና ተቋማቱ ወጣቶችን ማዕከል ያደረገ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርአት በመዘርጋት ለወጣቱ ጤና መሻሻል በጋራና በቅንጅት መስራት አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡
በአጠቃላይ የሴቶችና ወጣቶችን የጤና ሁኔታ ለማሻሻልና ተሳታፊነትና ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ በጤናው ሴክተር ትራንስፎሜሽን እቅድ ውስጥ የተቀመጡትን ዋና ዋና የትራንስፎሜሽን አጀንዳዎች በትኩረት መተግበር አስፈላጊና ወቅቱ የሚጠይቀው አቢይ ጉዳይ እንደ መሆኑ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ርብርብ ይጠይቃል፡፡

**"የሴቶች ሁለንተናዊ ጤና ለህዳሴያችን መሰረት ነው!!"**

# የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ከየት ወዴት?

በ1986ዓ.ም የወጣው ብሄራዊ የሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ የሴቶችን መብት ለማስጠበቅ እንዲሁም ለስርዓተ ጾታ ምላሽ ሰጪ ስራዎች በየደረጃው በሚገኙ መ/ቤቶች የስርዓተ ጾታ ጉዳይ ተካቶ መሰራቱን ለመከታተልና ለማስተባበር የሴቶች ጉዳይ በመምሪያ ደረጃ እንዲቋቋም መሰረት ጥሏል፡፡ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴርም በስሩ የሴቶች ጉዳይ መምሪያ በማቋቋም የሥርዓተ-ፆታ ተግባራትና መሰል እንቅስቃሴዎች ለረጅም ጊዜ ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ የመዋቅር ማሻሻያ (BPR) በሚሰራበት ወቅትም መምሪያው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ውስጥ ያልተካተተ ቢሆንም ሀገራዊ ፋይዳውን በማጤን ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ አዲስ ስያሜና መዋቅር ተሰርቶለታል፡፡ ስያሜውንም የሥርዓተ-ፆታ ዳይሬክቶሬት ተብሎ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ (managerial process) እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በመቀጠልም በአገር አቀፍ ደረጃ የወጣቶች ጉዳይ በሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲካተት በመደረጉ በ2005 ዓ.ም የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡ በመጨረሻም መዋቅሩም በጤናው ዘርፍ እንደመሆኑ መጠን ትርጉም ባለው ሁኔታ በወጥነት እንዲሰራ በማድረግና የሚጠበቅበትን ሀላፊነት ከሀገራዊ እቅዱ ጋር ተያይዞ እንዲሄድ ለማስቻል በተጠሪ ተቋማት፣በፌደራል ሆስፒታሎችና በክልል በሚገኙ የጤና ቢሮዎች ውስጥ እንዲቋቋሙ በማድረግ የአንድ እቅድና ሪፖርት የአሰራር ስርዓትን በማሳለጥ ዘርፈ ብዙ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡

**የስርዓተ ጾታ ጉዳይ ተቋማዊ ለማድረግ የተተገበሩ ጉልህ ስራዎች**

የስርዓተ ጾታ ጉዳይ የሰብአዊ መብት፣የፍትህ፣የልማት፣የመልካም አስተዳደር ጥያቄ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በሀገራችን ማንም ጠያቂ ማንም ተጠያቂ በማይሆንበት ስርዓት ለዘመናት ተንሰራፍቶ የነበረውን የስርዓተ ጾታ የተዛባ አመለካከትና ሲወርድ ሲዋረድ የመጣዉን አድሎአዊ ጫና ለማስተካከልና ዜጎችም የጤናውን ቱርፋት ተጠቃሚ በማድረግ ረገድ በአንድ ጀንበር ተሰርቶ የሚያልቅ ስራ አይደለም ይልቁንም ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑ እሙን ነው፡፡

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርም ይህን የተዛባ አመለካከትና የጤናውን ተጠቃሚነት የሚጎትት አስተሳሰብና ልምድ ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ለመፍታትና የዜጎች የጤና ተጠቃሚነት ለማሳደግ የስርዓተ ጾታ ማካተቻ ማንዋል በ1994 ዓ.ም አዘጋጅቶ ተግባራዊ በማድረግ በጤናው ዘርፍ ለውጦች ተመዝግበዋል፡፡ ይሁን እንጂ የጤና ጉዳይ በባህሪው ተለዋዋጭ፣ ከማህበረሰብ እድገት ጋር ተያያዥ በመሆኑና፣ በአዳዲስ አሰራሮች መሰረት በማድረግ በጤናው ሴክተር ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩና የምዕተ አመቱን ግቦች ላይ በጎ ተጽእኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ ፕሮግራሞችን መሰረት አድርጎ በ2006ዓ.ም የጤናው ዘርፍ የስርዓተ ጾታ ጉዳይ ማካተቻ ማንዋል ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩና አዳዲስ እውቀትን፣የአሰራር ዘይቤን በማካተት ክለሳ በማድረግ እየተሰራበት ይገኛል፡፡

በአሁኑ ወቅትም ይህ ማካተቻ ማንዋል በጤናው ዘርፍ ለውጦችን (ውጤቶች) እያመጣ ይገኛል፡፡ ለአብነትም በሚ/ር መ/ቤት ደረጃና በተጠሪ ተቋማት በክልሎች የስርዓተ ጾታ ፅንሰ ሀሳብ የወጣቶች ጉዳይ ማካተት ምንነትና አስፈላጊነት እንዲሁም የማካተቻ ስልቶቹን አስመልክቶ አመራሮችና ባለሙያዎች ግንዛቤ መጨበጣቸው በሴክተሩና በተጠሪ ተቋማቶቻችንና ክልሎች ስርአተ ጾታን ያካተተ እቅድ፣ሪፖርትና መረጃዎች የመተንተንና የማደረጀት የመጠቀም ልምድ ማደጉና በየክልሉ መዋቅሩ እየሰፋ መሄዱ የሴቶችና የወጣቶችን ጉዳይ ተቋማዊ ለማድረግ የተደረገው ጥረት በአጭር ጊዜ የተገኙ ውጤቶች ናቸው፡፡ ይህም በጤናው ዘርፍ እየተሰራ ያለው ስራ በትክክለኛ መስመር ላይ መሆኑን አመላካች ነው፡፡ በተጨማሪም የስርዓተ ጾታ ማካተቻ ማንዋሉ በዘርፉ ለማስረፅ እንዲቻልና ቀጣይነት እንዲኖረው የሀላፊዎችና የባለሙያ የስርዓተ ጾታ ግንዛቤቸውን ለማሻሻል የጤናው ዘርፍ የስርዓተ ጾታ ማሰልጠኛ ማንዋል በሶስት ዘርፍ (የአሰልጣኝ መመሪያ ፣የሰልጣኝመመሪያ ፣የሰልጣኝ ማስታወሻ ) በማዘጋጀት ማሰራጨት ተችሏል፡፡

**ሴቶች ወደ አመራር ከማምጣት ጋር ተያይዘው የተከናወኑ ክንውኖች**

ሃገራችን የሴቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ዋስትና የሰጡ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ድንጋጌዎች ፈራሚ ከመሆኗ በተጨማሪ የዘላቂ ልማት ግብ ለማሳካት ከሚተጉ አገራት መካከል አንዷ ነች፡፡ በመርህ ደረጃ አገራችን ስምምነቶችን መፈረሟና የዘላቂ ልማት ግቦቹን ተቀብላ ለማስፈጸም መትጋቷ በሕግ ደረጃ የሴቶችን መብት ለማስከበር ያላትን ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ያሳያል፡፡ ሃገራችን የፆታ መድሎን ለማስቀረት በተለያዩ ብሔራዊና ክልላዊ ፖሊሲዎች ውስጥ የሴቶችን ጉዳይ እንዲካተት አድርጋለች፡፡ የስርዓተ ፆታ እኩልነት መኖሩን በየሴክተሩ ለማረጋገጥ የሴቶች ብሔራዊ ፖሊሲ ተቀርጾ በመፈፀም ላይ ሲሆን፣ ተግባራዊ አፈጻጸሙን ለማጠናከር ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ተተግብሯል፡፡ ሃገሪቱ ለሴቶችና ሕፃናት መብት ያላትን ቁርጠኝነት በሕገ መንግሥቱ የደነገገች ሲሆን፣ በዚሁ መሰረት የቤተሰብ ሕጉና የወንጀለኛ መቅጫ ህግ እንዲሻሻል አድርጋለች፡፡ በተለይ ደግሞ በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 35 ሴቶች ሕገ መንግሥቱ በሰጣቸው መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድ ፖለቲካዊ ተሳትፎን ጨምሮ ከወንዶች ጋር እኩል መብት እንዳላቸው አረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም በሕገ መንግሥቱ ሴቶች የአዎንታዊ ዕርምጃ ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ የተደነገገ ሲሆን፣ ዕርምጃው ከሚፈጸምባቸው ዘርፎች አንዱ የፖለቲካው ዘርፍ መሆኑ በሕገ መንግሥቱ ተደንግጓል፡፡ ሌላው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድና ብሔራዊ የሰብዓዊ መብት የድርጊት መርሀ ግብርም ሴቶች በፖለቲካዊ ተሳትፎአቸው ከወንዶች እኩል ተጠቃሚ የሚሆኑበትን አሠራር አካቷል፡፡

**በዋናው ግቢ የሚገኙ የከፍተኛ፣ መካከለኛና ዝቅተኛ አመራር ደረጃ ማሳያ**

| ተ.ቁ | የስራ ሀላፊነት | ወንድ | ሴት | የሴቶች ተሳትፎ በ% |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሚኒስትር | 1 | 0 | 0% |
| 2 | ሚኒስትር ዴኤታ | 2 | 0 | 0% |
| 3 | የሚኒስትር ጽ/ቤት ሀላፊ | 2 | 1 | 33% |
| 4 | ዳይሬክተር | 15 | 5 | 25% |
| 5 | ረዳት ዳይሬክተር | 9 | 5 | 35% |
| 6 | የቡድን መሪ/ኬዝ ቲም መሪ | 38 | 19 | 33% |
| | ድምር | 67 | 30 | |

በ2009ዓ.ም በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከሚገኙ የመካከለኛ ደረጃ ቦታዎች ለአብነት ብንመለከት በዳይሬክተር ደረጃ የሴቶች ተሳትፎ 25% ወንዶች 75 % ፣ረዳት ዳይሬክተር ደረጃ ሴቶች ተሳትፎ 35%፣ወንድ 65%፣ቡድን መሪ/ ኬዝቲም አስተባባሪ ሴት ተሳትፎ 33% ወንድ 67% ሆነው ይታያሉ፡፡ ከላይ የተጠቀሰው አሀዝ እንደሚያሳው የሴቶች ተሳትፎ በከፍተኛና በመካከለኛ አመራር ደረጃ በአንጻራዊነት አበረታች መሆኑ የሚያሳይ ሲሆን ይህ አሀዝ እንዳይቀንስና ከዚህም በላይ ለመጨመር በርትቶ መስራት እንደሚጠይቅ አመላካች ነው፡፡

**በተጠሪ ተቋማት የሴቶችን የአመራር ደረጃ የሚያሳይ ትንተና**

- ኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲቲዩት በከፍተኛና በመካከለኛ አመራር ደረጃ የሴቶች ተሳትፎ 10% ሲሆን በዝቅተኛ አመራር ደረጃ ( ቡድን መሪና ኬዝቲም አስተባባሪ ) 22% ፤
- ኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድሀኒት፣የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን በከፍተኛና በመካከለኛ አመራር ደረጃ የሴቶች ተሳትፎ 18% በዝቅተኛ አመራር ደረጃ ( ቡድን መሪና ኬዝቲም አስተባባሪ ) 25% ፤
- የፌደራል ኤች.አይ.ቪ.ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት በከፍተኛና በመካከለኛ አመራር ደረጃ የሴቶች ተሳትፎ 8% በዝቅተኛ አመራር ደረጃ ( ቡድን መሪና ኬዝቲም አስተባባሪ ) 33% ፤
- መድሀኒት ፈንድ አቅርቦት ኤጀንሲ በከፍተኛና በመካከለኛ አመራር ደረጃ የሴቶች ተሳትፎ 14% በዝቅተኛ አመራር ደረጃ ( ቡድን መሪና ኬዝቲም አስተባባሪ ) 7% ፤
- ብሄራዊ ደም ባንክ አገልግሎት በከፍተኛና በመካከለኛ አመራር ደረጃ የሴቶች ተሳትፎ 0% በዝቅተኛ አመራር ደረጃ ( ቡድን መሪና ኬዝቲም አስተባባሪ ) 0%፤
- ጤና መድህን በከፍተኛና በመካከለኛ አመራር ደረጃ የሴቶች ተሳትፎ 0% በዝቅተኛ አመራር ደረጃ (ቡድን መሪና ኬዝቲም አስተባባሪ ) 100% ፤
- መላው አፍሪካ ስጋ ደዌ መከላከያና ትምህርት መስጫ ማእከል (አለርት) በከፍተኛና በመካከለኛ አመራር ደረጃ የሴቶች ተሳትፎ 18% በዝቅተኛ አመራር ደረጃ ( ቡድን መሪና ኬዝቲም አስተባባሪ ) 24% ፤
- ቅዱስ ጴጥሮስ ቲቢ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በከፍተኛና በመካከለኛ አመራር ደረጃ የሴቶች ተሳትፎ 23% በዝቅተኛ አመራር ደረጃ ( ቡድን መሪና ኬዝቲም አስተባባሪ ) 53% ፤
- ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ በከፍተኛና በመካከለኛ አመራር ደረጃ የሴቶች ተሳትፎ 41% በዝቅተኛ አመራር ደረጃ ( ቡድን መሪና ኬዝቲም አስተባባሪ ) 24% ፤
- አማኑኤል አእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በከፍተኛና በመካከለኛ አመራር ደረጃ የሴቶች ተሳትፎ 23% በዝቅተኛ አመራር ደረጃ ( ቡድን መሪና ኬዝቲም አስተባባሪ ) 22% ፤

ከዚህ በላይ ያለው አሀዝ እንደሚያሳው የሴቶች በአመራር ደረጃ በተጠሪ ተቋማቶቻችን (ሆስፒታልና ኤጀንሲ) በመካከለኛ አመራር ደረጃ ቁጥራቸው እጅግ አናሳ ሲሆን ብሄራዊ ደም ባንክ አገልግሎትና ጤና መድህን ኤጀንሲዎቻችን የሴቶች ተሳትፎ የሌለበት ነው በተቃራኒው ደግሞ በዝቅተኛ አመራር ደረጃ የተወሰነ ወጣ ገባ ያለ የሴቶች የተሳትፎ አሀዝ ያሳያል፡፡

ባጠቃላይ ይህ በዝቅተኛ የአመራር ደረጃ ላይ ያለውን የተተኪ ሴቶች ቋት በመጠቀም ለመካከለኛ አመራር በማብቃት ረገድ ሴቶችን ወደ አመራርነት ለማምጣት የተቋሙ ከፍተኛ አመራሮች አቅደዉ መስራት እንዳለባቸው አመላካች ጉዳይ ነው፡፡

**በዋናው መ/ቤትና በተጠሪ ተቋማት የሴቶች የአመራር የተሳትፎ ደረጃ በጾታ ስብጥር**


የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ከተቋቋመለት አላማና የስራ ወሰን በመነሳት ካሉት አስር እስትራቴጅክ እርምጃዎች አንዱ ሴቶችን ማብቃት በሚል አቅዶ እየሰራ ነው፡፡ በዚህም ሴት አመራሮች ማለትም ዳይሬክተር፣ረዳት ዳይሬክተር፣ቡድን መሪ / የኬዝቲም መሪ ለሆኑ ሴት ሀላፊዎች ፍላጎት መሰረት ያደረገ ትራንስፎርሜሽን አመራርነት (Transformation leadership) ፣የአመራር ጥበብ፣የቡድን ግንባታ፣ በራስ መተማመን በሚል ርእስ በየደረጃው ስልጠናዎችን በማዘጋጀት የሴቶችን አመራርነት ክህሎትና እውቀት በማሻሻልና ተተኪ ሴት አመራሮች ለማፍራት እንዲቻልና ሴክተሩም በፖሊሲ የክለሳ ረቂቅ በጤናው ዘርፍ የአስተዳደርና አመራር ላይ የሴቶችን እኩል ተሳታፊ ለማድረግ በጤና ዘርፍ የሚኖሩ የሴት አመራሮችን ቁጥር ከወንዶች እኩል ለማድረግ ለያዘው ስልት ተደጋጋፊ እንዲሆን የበኩሉን እየተወጣ መሆኑን ያሳያል፡፡

**ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ ከመስራት ጋር ያለ ተሞክሮ**

በሴቶችና ወጣቶች የጤና ተጠቃሚነት ብሎም የተዛባ ስርዓተ ጾታ አስተሳሰብን ለመፍታተትና በጤናው ዘርፍ የታቀደውን እቅድና የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካት የበርካታ ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡

በመሆኑም የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ካሉት 10 እስትራቴጅክ እርምጃዎች አንዱን ቅንጅታዊ አሰራርን ማሳደግ ሲሆን ዳይሬክቶሬቱ ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ማለትም ከተቀናጀ የቤተሰብ ጤና ፕሮግራም፣ከአለም ጤና ድርጅት፣ከኢትዮጵያ ጽንስና ማህፀን ባለሙያዎች ማህበር ፣የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኛ ማህበር፣ሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ ወዘተ ጋር እየሰራ ይገኛል፡፡

በዚህ ቅንጅታዊ አሰራር ለጤናው ዘርፍ building block ትርጉም ባለው መልኩ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ ለአብነትም የጤናው ዘርፍ የስርዓተ ጾታ ማካተቻ ማንዋል፣የጤናው ዘርፍ የስርዓተ ጾታ ማሰልጠኛ ማንዋል፣ ወሲባዊ ጥቃትን የመከላከልና ምላሽ የመስጠት የአተገባበር ስርዓት ሰነድ፣የጾታዊ ጥቃት አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ማሰልጠኛ ማንዋል፣የአካል ጉዳተኞች ማካተቻ ማንዋል፣በጤናው ዘርፍ የትራንስፎርሜሽ እቅዱን ለማሳካት በወረዳና በጤና ተቋም ደረጃ በቀላሉ ሊጠቀሙበት የሚችሉበትና ለአያያዝ ቀላል (pocket guide) በማድረግ የስርአተጾታ ማካተቻ መመሪያ፣ የወንዶች አጋርነት፣የስርዓተ ጾታና ተግባቦት ግንዛቤ ማስጨበጥ ስራዎች የሚጠቀሱ ናቸው፡፡





ማንኛዋም ነፍሰጡር እናት ነፍሰጡር መሆንዋን ካወቀችበት ጊዜ አንስቶ የቅድመ ወሊድ ህክምና ክትትል መጀመር አለባት/ ይጠበቅባታል፡፡ የቅድመወሊድ ክትትል ለነፍሰጡር እናቶችና ቤተሰቦቻቸዉ ስለጤናማ እርግዝና፣ወሊድና የድህረወሊድ ክትትል በተለይ ስለጨቅላ ህፃን እንክብካቤ፣ ስለጡት ማጥባትና ስለወደፊቱ የእርግዝና ሁኔታ መረጃና ምክር ለመስጠት ይረዳል፡፡ የአለም ጤና ድርጅት እንዲሁም የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በአዘጋጀዉ ሃገር አቀፍ የቅድመወሊድ መመሪያ እንድንከተል የሚያዘዉ አንዲት እናት ነፍሰጡር መሆንዋን ካወቀችበት ጊዜ አንስቶ እስክትወልድ ድረስ አራት ጊዜ የቅድመ ወሊድ ክትትል ማድረግ ይገባታል፡፡ ከዚህ አብይ የጤና ጉዳይ ጋር ተያይዞ እንደ አዉሮፓዉያን የዘመን አቆጣጠር ከ 2000 እስከ 2016 በተሰሩ ሐገር አቀፍ የስነ ሕዝብና የጤና ጥናቶች የቅድመ ወሊድ ክትትል አገልግሎት ተጠቃሚ እናቶች ቁጥር በ 2000 እ.አ.አ 27% ከነበረበት በ2016 62% መድረስ ችሏል፡፡




ኢትዮጵያ በአፍሪካ ደረጃ ብዙ ህዝብ ከሚቆጠርባቸው አገራት በሁለተኛ ደረጃ የምትገኝ አገር ናት። የወሊድ መጠኑ በአንድ ሴት 4.1 ሲሆን የእናቶች ሞት መጠን ደግሞ ከ100,000 በህይወት ከሚወለዱ ህፃናት ውስጥ በ1990 እ.ኤ.አ 1400 ከነበረው በ2016 ወደ 412/100,000 በዚህም 71% መድረስ ችሏል፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች አብዛኞቹ እናቶች ልጆቻ ቸውን የሚወልዱት በቤታቸው ሲሆን ወደሕክምና ተቋም በመምጣት በሰለጠነ ሰው ኃይል የሚወልዱት 28/በመቶ ብቻ ናቸው። ይህም ከአገልግሎት፣ ከእውቀት ማነስ፣ዝቅተኛ ከሆነ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አቅም እንዲሁም ተገቢውን አገልግሎት ከሕክምና ተቋማት ማግኘት አለመቻላቸውን ምክንያት በማድረግ ነው። ይህንኑ መሰረት በማድረግም የጤናዉ ዘርፍ የአምስት አመት ስትራጂክ እቅድ ማለትም ከ2015-2020 ትኩረት ከሚደረግባቸው ተብለው ከተለዩት ጉዳዮች ዉስጥ የእናቶች በህክምና ተቋም መውለድ እንዲሁም በሰለጠነ ባለሞያ መታገዝ አንዱ የትኩረት አቅጣጫ ነዉ፡፡ የስነ ሕዝብና የጤና ጥናቶቹም እንደሚያሳዩት በሰለጠነ ባለሞያ በህክምና ተቋም ላይ የሚወልዱ እናቶች እጅግ ዝቅተኛ ከነበረበት ከ 6/መቶ በ 2000 አሁን ወደ 28/መቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

ዘመናዊ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ተጠቃሚ ሴቶች




የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት የጤና ጥቅም አለው ሲባል ወሊድን መመጠን ከሚለው ብቻ ሳይሆን ካንሰርን ኢንፌክሽንን ፣በወር አበባ ጊዜ ሕመምን መቀነስ እና በተለይም የወር አበባ በሚታወቅ ጊዜ እንዲመጣ ማስቻሉ የአገልግሎቱን ጠቀሜታ ከፍ ያደርገዋል፡፡ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎትን ከኢኮኖሚ አንጻር መመልከት ማለት ከምእተ አመቱ የልማት ግቦች በመጀመሪያው ላይ ከሚታየው ድህነትን መቀነስ ረሀብን ማስወገድ ከሚለው እሳቤ ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ ቤተሰብ በእቅድ ላይ ከተመሰረተ እና የቤተሰቡን መጠን ከወሰነ ለቤተሰቡ በሚያቀርበው ሀብት በበቂ ሁኔታ ለማስተዳደር ያስችለዋል፡፡ሴቶች የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴ ተጠቃሚ በሚሆኑበት ጊዜ ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ያስችላቸዋል፡፡ በዚህ እሳቤ ሀገራችን በቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ዘርፍ አበረታች ለውጥ አስመዝግባለች። በዚህም መሠረት ዘመናዊ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴ ተጠቃሚነት ባለፉት አስርት ዓመታት ውስጥ ከእጥፍ በላይ ጭማሪ ያሳየ ሲሆን፤ ይኸውም በ2005 ዓ.ም ከነበረበት 14 በመቶ በ2016 ወደ 35 በመቶ ከፍ ብሏል። በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ከሶስት ሴቶች መካከል አንዷ ዘመናዊ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴ ተጠቃሚ ናት፡፡





ወ/ሮ ተስፋዬነሽ ለማ
በሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር የሴቶች ጉዳይ ማካተትና
ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

መ/ቤታችን ሴክተሮችን በመደገፍ ሂደት ለዕድገት ተኮር ሴክተሮች ቅድሚያ በመስጠት የሴክተርና የሴ/ወ/ጉ/ዳ ዓመታዊ ዕቅድና ሪፖርት ከሥርዓተ ፆታ ጉዳይ ማካተትና ሴቶች ተጠቃሚነት አኳያ በመገምገም ግብረመልስ መስጠት፣የሥርዓተ ፆታ ተቋማዊነት ለማጠናከር በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀረፁ የሥርዓተ ፆታ ማካተቻ፣ ትንተናና ኦዲት መመሪያዎችን ተደራሽ በማድረግ፣ ተቋማዊ አቅም ለማጐለበት በተካሄዱ የስርዓተ ፆታ ስልጠናዎች በማሳተፍ፣ በሴክተሩ የሥርዓተ ፆታ ስትራቴጂና ማካተቻ ማኑዋል ዝግጅት የኮሚቴ አባል በመሆን የአጋዥነት ሚናውን ሲወጣ ቆይቷል፣ በተጨማሪም በሴክተሩ ተጠሪ መ/ቤቶችና የክልል ጤና ቢሮዎች የሥርዓተ ፆታ ባለሙያዎች የጋራ ፎረም ዕቅድና አፈፃፀም መድረክ በመገኘት ሙያዊ ተሳትፎ በማድረግ የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሴቶችንና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ሴክተር ተኮር የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓትን በጤናው ሴክተር ለመዘርጋት ከመንግስት፣ ከአጋሮችና ከሲቪክ ማህበራት የተውጣጡ የሥራ ቡድኖችን /ኮሚቴዎችን በማዋቀር የሴክተሩን የሥርዓተ ፆታ ስትራቴጂ እንዲሁም ደረጃውን የጠበቀ የጤና ሴክተር የሥርዓተ ፆታ ማካተቻ ማኑዋል በማዘጋጀት በስፋት በየደረጃው በማስተዋወቅ ስልት ነድፎ በየደረጃ እንዲተገበር መደረጉና በጤና ፖሊሲ ክለሳ ወቅትም የሴቶች ጉዳይ በአግባቡ ምላሽ እንዲያገኝ መደረጉ በጉልህ የሚጠቀሱ ተግባራት ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በሴክተሩ በሚገኙ ተጠሪ መ/ቤቶችና የክልል ጤና ቢሮዎች የሥርዓተ ፆታ ባለሙያዎች የጋራ ፎረም በመመስረት ከዕቅድ አቅጣጫ እስከ ትግበራና አፈፃፀም ያለውን በመድረክ መገምገምና የማስፈፀም አቅም በማጐልበት ሴቶች ከሴክተሩ በየደረጃው ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች አበረታች ናቸው፡፡

በሀገር ደረጃ የሴቶች ተጠቃሚነትን በጤናው ዘርፉ ስናይ የባለፉት ዘመናት የነበረው የሴቶች ተጠቃሚነት ማነፃፀሩ ጠቃሚ ነው፡፡ በህገ መንግስቱ እና በአዋጅ ቁጥር 916/2008 የአስፈፃሚ ማቋቋሚያ በሁሉም ተቋማት የሴቶች ጉዳይ አካተው እንዲሰሩ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡



ክብርት ወ/ሮ ሳሃርላ አብዱላሂ
በኢፌዲሪ ህዝብ ተወካዮች ም/ቤት
የሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ

ከዚህ በመነሳት በጤናው ዘርፍ የሴቶችን ተጠቃሚነት ስንመለከት እናቶች በሆስፒታል እንዲወልዱ መደረጉ እና አንድም እናት በወሊድ ምክንያት እንዳትሞት እየተደረገ ያለውየስራ እንቅስቃሴ፣የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ሙሉ በሙሉ ሴቶች መሆናቸውና የስናቶችን ጤና በቅርበት መከታተል መቻላቸው፣ በሀገር ደረጃ ከፍተኛ እና አመርቂ ውጤት የተመዘገበበት ነው ማለት ይቻላል፡፤ ነገር ግን ይህን ለማሳካት ሴቶች በልማት ቡድን እንዲደራጁና ስለራሳቸው ጉዳይ
በጤናው ዘርፍ እንዲያወሩና እናቶች በምጥ ጊዜ እንደየአከባቢያቸው ባህል እና እሴት ተጠብቆ የእናቶች ማቆያ ቤቶች በጤና ጣቢዎች እንዲገነቡ መደረጉ ከየትኛውም ጊዜ በተሻለ የተከናወኑ ተግባር ናቸው፡፡ በተጨማሪም ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ልይ የተሰሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ሴቶች በጤናው ዘርፍ ተጠቃሚነታቸው ያሳያል፡፡ ይህን ስል ግን የሴቶች ጤና ችግር በሚፈለገው ደረጃ ተቀርፏል ማለት አይቻልም ነገር ግን እየተሰሩ ያሉ ስራዎች በዚህ ማስቀጠል ከተቻለ የተሸለ ሊሆን ይችላል፡፡

በጤና ጥበቃ ሚኒስትር የሴቶችና ወጣቶች ዳይሬክቶሬት የሴቶች ተሳትፎ ተጠቃሚነት በጤናው ዘርፍ ሴቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ የወጡ አዋጆች እና ህጎች ተደራሽነታቸውን ከማረጋገጥ፣የፆታዊ ጥቃት እና በሀገር አቀፍ ደረጃ አገራችን የገባችውን ስምምነቶች ለማስፈፀም በ2030 ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ለማሰወገድ በእቅዳቸው አካተው እየሰሩ ሲሆኑ እንደ ህ/ተ/ም/ቤት በክትትልና ግምገማ የአፈፃፀም ሪፖርቱንም ሆነ በዓመታዊ የምክክር መድረካቸው ላይ በመገኘት እንዳየነው ከሁሉም ክልሎች እና ከተጠሪ ተቋማት ጋር በጋራ አፈፃፀማቸውን የመገምገምና በጋራ የማቀድ እንዲሁም ምርጥ ተሞክሮዎችን ቀምሮ የማስፋት አሰራር መኖሩ ክፍተቶችን ለመለየትና ድጋፍ ለማድረግ እንዲሁም የተሻለ ውጤት ያስመዘገቡትን እውቅና እየሰጡና እያበረታቱ የመሄድ ሂደቱ ተጠናክሮ በመቀጠል የተሸለ ስራ ለመስራት ያግዛል፡፡ በተጨማሪም በጤናዉ ዘርፍ ለአካል ጉዳተኞች ትኩረት ተሰጥቶት ፍትሃዊነትን ለማስፈን እንቅስቃሴ መኖሩ ሊበረታታ የሚገባ ጉዳይ ነው፤በአጠቃላይ ብዙ ለሴቶች ጤና ተጠቃሚነት የሚያግዙ ስራዎችን እየሰራ ያለ ዳይሬክቶሬት ሲሆን ሴቶችን ወደ አመራር ለማምጣት ተጨማሪም ባይሆን ሳይቋረጥ በየተጠሪ ተቋማትና በየክልል ጤና ቢሮ የሚገኙ ሴቶችን አቅም ግንባታ ስልጠናዎች ፤በአካዳሚካል ሴቶችን እያበቁ በራስ መተማመናቸውን እያዳበሩ እንዲሄዱ ማድረግና በመረጃ የተደገፈ እቅድ በማቀድ የሴቶች ውሳን ሰጪነት አመላካች እያስቀመጡ የመሄዱን ጉዳይ

## 6ኛዉ አመታዊ የጤናዉ ዘርፍ የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ መዋቅሮች የምክክር መድረክ ተሳታፊዎች ጉብኝት በታላቁ የሕዳሴ ግድብ ሰኔ 2008



# አዝናኝ ቁምነገር አዘል ወጎች እዉነታዎችና አባባሎች

## እናስተዋውቃችሁ
## ኢትዮጵያና የመጀመሪያ እንስቶቿ



Wzro Assegedech Assefa

ወ/ሮ አሰገደች አሰፋ በ1950ቹ የተለያዩ መሰናክሎችን በማለፍ በወቅቱ ሙሉ ለሙሉ የወንዶች ሙያ ሆኖ የነበረውን የአውሮፕላን በረራ ትምህርት በመውሰድ ከኢትዮጵያ ከዛም አልፎ ከአፍሪካ የመጀመሪያዋ ሴት ፓይለት ለመሆን በቃች፡፡ ለአሁኑ ሴት ወጣቶች ካስተላለፈቻአቸው መለልዕክቶች መካከል "ወጣት ሴቶች ባላችሁ ችሎታ የራስ መተማመንና እምነት ሊኖራችሁ ይገባል" የሚል ይገኝበታል፡፡

ምንጭ፡-http://www.ethiopianreview.com/index/51349

## ማህበራዊ የአፍ ወለምታዎች

እንዴት ከረማቸሁልኝ ወዳጆቼ...ያው እንደልማዳችን እናውጋ ዛሬ የማወጋችሁ ስለ አፍ ወለምታ ነው፡፡ እንዲያው ለምዶብን ሳናስበው ስለምንናገራቸው አፍራሽ ንግግሮችና አባባሎች በተለይም ስለ ሴቶች፣ህፃናትና ወጣቶች የሚነገሩ ልማዳዊና አፍራሽ አባባሎች የታዘብኩትን ላውጋችሁ፡፡ ማህበረሰባችን ስለ ፆታ እኩልነት ያለው ግንዛቤ እየተሻሻለ ቢሆንም ያቺ የአፍ ወለምታችን ዛሬም አለች፡፡

በቀደም ለታ አውቶብስ ውስጥ ሁለት ጎረምሶች እየጮሁ ይሰዳደባሉ፡፡ ታዲያ መጣላት ብርቅ ነው እንዳትሉኝማ፡፡ ነገሩ ወዲህ ነው... ያበሳጨኝ የሌላው ተሳፋሪ አስተያየት ነው... "ምን እነዚህ ወንድ አሰዳቢ..... ሴታሴት ነገር ናቸው" ይላል በጣም ተናድጄ መጮህን የሴት ማን አደረገው አለኩኝ አንዷት አሮጊት እየሳቁ "አሄሄ.. የወንዶችማ ተግባር ሜዳ ወርዶ በሽመል እየተሞሻለቁ ጥሎ መፎከር ነው እንጅ ጯሂዋማ ሴት ናት" አሉኝ፡፡ እንዴት ወንዶች በተሳደቡት እኛ ሴቶች እንዘለፋለን ደግሞስ ድብድብ አልኩኝ፡: "ሴት ምን ብታውቅ በወንድ ያልቅ" አሉ አንድ አዛውንት፡፡ አንድዋ እናት ደግሞ "ዝም በይ ልጄ ሴት ከማጀት ወንድ ከችሎት ሲባል አልሰማሽም የምትናገሪው እውነት እንደሆነ ባውቅም በአደባባይ ከወንዶች ጋር መነታረክሽን አልወደድኩልሽም " አሉኝ፡፡

እጅግ ተከፍቼ ሳለሁ ሁለት ወጣት ፍቅረኛሞች እየተቀባበሉ የልቤን አደረሱልኝ፡፡ "የጉንዳንን ጉልበት የሴትን ብልሀት ይስጠን ከተባለ ቆየኮ...ንግስት ሳባን ዘነጋቻኋት ኪሊዮፓትራስ ብትሆን..." በቃ ቀወጡ...

"ተባረኩ ልጆቼ ስራችሁ ምንድነው?" አሉ አንድ አዛውንት "ሀኪሞች ነን" አለ ወንዱ "እሺ ዶክተርዬ ነርሷ ጓደኛህ ናት?" አሉ አዛውንቱ እንግዲህ በሳቸው አስተሳሰብ ሴት ከነርስነት አታልፍም ለማለት ነው፡፡ ይህንን የአውቶብስ ውስጥ ገጠመኜን ለቤተሰቦቼ ስነግራቸው ሁሉም በአቋሜ ተደሰቱ... አባቴ ግን ያሞገሰኝ መስሎት አፉን ወለም አለው..እንዲህ አለኝ... "አይ የኔ ልጅ አንቺ እኮ የሴት ወንድ ነሽ !" ጉዴ ቤቴም ገብቷል ለካ....

እናንተዬ ይሄ የአፍ ወለምታችን ወደ ታሪክ ፀሀፊዎችም ደርሷል.... የቋራውን ቴዎድሮስ ያሞገሱ መስሏቸው የሴትን ክብር ያንኳሰሱበት ግጥም እንዲህ ይላል

"መቅደላ ካፋፉ ጨኸት በረከተ
የሴቱን አናውቅም ወንድ አንድ ሰው ሞተ"

እያሉ የተዋበችን ታማኝነት ስተው የጣይቱን ጀግንነት ዘንግተው

እናንተዬ ይሄ ማህበረሰባዊ የንግግር ግድፈት ህፃናትንም ለማሸማቀቅ ይዳዳዋል እኮ.... "ለልጅ ከሳቁለት ለውሻ ከሮጡለት".... "ያለ እድሜው ያደገ"... ምናምን እያልን በዝምታ ስንጨቁናቸው ምን ብለው እንደሚያማርሩ ታውቃላችሁ "በሁለት አመታችን እየተንተባተብን ቋንቋ እንድናውቅና መናገር እንድንችል ካደረጉ በኋላ በአራት አመታችን ዝም በሉ ይሉናል" እያሉ ህፃናቱ ያማርራሉ፡፡

አሁን አሁንማ ህፃናቱን ይዛችሁ እንዳትመጡ የሚሉ ሙሽሮች እየበዙ ነው "ህፃናት ወደኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው" እስኪባል በፈጣሪ እንዳልተነገረላቸው.... የልጅነት ጊዜ ሳናሳልፍ ጎልምሰን የተወለድን ይመስል ልጆችን እንዲህ ማንኳሰስ ምን ይባላል?

ይሄ አፋዊ ወለምታችን ወጣቶችንም ይወርፋል እኮ.. ልጅ እያሱን ስልጣኔን ባስፉፋ ልጅ ጨቅላ ብለን አባረርነው እኮ...አሁን እስኪ.....

የፍየል ወጠጤ ልቡ ያበጠበት
እንዋጋ ብሎ ለነብር ላከበት

መባል ነበረበትን?... ወጠቴነት የተባለው እኮ ወጣትነት ነው፡፡ ለነገሩ ወጣቶችም የዋዛ አይደሉም ወጣቶች የነገ ሀገር ተረካቢዎች የነገ ባለ ራዕዮች የነገ የነገ... የሚለው አባባል ይቁምልን ምክንያቱም ዛሬም የልማቱና የአመራሩ አካል ነንና.... ይልቁንስ የነገ ምናምን የሚባለው አባባል ...ዱቤ ነገ እንጅ ዛሬ የለም እንደሚለው ፉገራ ነው.... ብለዋል አሉ...

ምንጭ እሰማዔል ከድር እነደፃፈው (ለመፅሄት)

## በአሁኑ ሰዓት የስርዓተ ፆታ እኩልነት እንደሚያስፈልግ የሚያረጋግጡልን ሰባት አስደንጋጭ እውነታዎች

1. በ2017 በመላዉ አለም 21 ሴቶች ብቻ በሀገር መሪነት መቀመጣቸው
2. ከ150 ሀገራት በላይ ቢያንስ አንድ ሙሉ ለሙሉ ፆታዊ አድልኦ መኖሩን አመላካች ህግ መኖሩ
3. በአንድ ደቂቃ ውስጥ 28 ልጃገረዶች ለአቅመ ሄዋን ከመድረሳቸው በፊት መዳራቸው
4. ከ3 ሴቶች ውስጥ አንድ ሴት በህይወት ዘመኗ የአካል ወይንም የወሲብ ጥቃት ማስተናገዷ
5. በአብዛኛዉ ሀገራት በተመሳሳይ ስራ ሴቶች የሚያገኙት ደምወዝ የወንዶችን ከ60 እስከ 75 መካከል ያለውን ማግኘታቸው
6. በአለም ላይ ከሚገኘው 781 ሚሊዮን የሚጠጉ ያልተማሩ አዋቂዎች ውስጥ ሁለት ሶስተኛው ሴቶች መሆናቸው
7. በአሁኑ ሰጫት 63 ሚሊዮን ልጃገረዶች ትምህርት ቤት መሄድ የሚያስፈልጋቸው መሆኑ፡፡

ምንጭ፡-https://www.globalcitizen.org/en/content/shocking-facts-gender-inequality-international-wom/

## ምልከታዎች
### ምቹ ክሊኒክ በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ




የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ምቹ ክሊኒክ ከፍቶ አገልግሎት መስጠት ከጀመረ ዘጠኝ ወራትን አስቆጠረ፡፡ የሚድዋይፍሪ ባለሙያና የአገልግሎት ሰጭ ባለሙያ የሆኑት አቶ ኢብራሄም አህመዲን እንደገለፁት ምቹ ክሊኒኩ የአገልግሎት መስጫ ሰባት ክፍሎች ሲኖሩት የሚሰጣቸው አገልግሎቶችም የምክርና የህክምና አገልግሎት ሲሆን የሚሰጣባቸው ዘርፎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት፣የማህፀን ጫፍ ካንሰር ምርመራና ህክምና፣የወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ፣ቅድመ ወሊድና ድህረ ወሊድ አገልግሎት፣ህጋዊ ፅንስ ማቋረጥ እና የመሳሰሉትን ሲሆን አገልግሎቱ ለሰባት ቀናት ለ24 ሰዓት ይሰጣል፡፡ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ከመላው ኢትዮጵያ የሚመጡ ሲሆን በብዛት ግን የአዲስ አበባ እና የአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ነዋሪዎች ናቸው፡፡

ወሲባ ጥቃትን በተመለከተ አገልግሎት መስጠት ከጀመረ 3 ወራትን ያስቆጠረ ሲሆን ለጥቃት ተጎጅዎች ጥቃቱ ከተፈፀመ በ72 ሰዓታት ውስጥ መከላከል ለሚቻሉ ልዩ ልዩ ምርመራ፣የቅድም መከላከል ህክምናዎች እንዲሁም የካውንስሊንግ አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን ከዛም በማስቀጠል የህግ ድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ ከፖሊስ ጋር አብረው እንደሚሰሩ አስታውቀዋል፡፡ አገልግሎቱን ከተጀመረ ጀምሮ ተጠቂዎች ከ8-18 ዓመት ያሉ ህፃናት ሲሆኑ የሴቶች ድርሻ ከ60-70% ያለውን ሲይዝ ወንድ ህፃናት 10 ፐርሰንቱን ይሸፍናል፡፡

## የሴቶችና ህፃናት የተቀናጀ እንክብካቤ እና ፍትህ ማዕከል የአንድ መስኮት አገልግሎት በጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታል




የጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታል የሴቶችና ህፃናት የተቀናጀ እንክብካቤ እና ፍትህ ማዕከል ከፍትህ ሚኒስቴር፣ትምህርት ሚኒስቴር፣ጤና ጥበቃ ሚኒስተር፣ሴ/ህ/ወ/ገ/ ሚኒስቴር ፣ፖሊስ ኮሚሽን፣አዲስ አበባ ጤና ቢሮ እና የመሳሰሉት ግብረሀይል በማቋቋም ተሞክሮውን ከደቡብ አፍሪካ ኬፕ ታውን በመቀመር በዩኒሴፍ የገንዘብ ድጋፍ ተመስርቶ ከ2004ዓ.ም ጀምሮ የአንድ መስኮት አገልግሎት መስጠት መጀመሩን የሆስፒታሉ ባለሙያ የሆኑት ዶክተር ደረጀ አለማየሁ ገለፁ፡፡

ማዕከሉ ወሲዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶችና ህፃናት ነፃ የህክምና፣የፍትህ፣የስነ-ልቦና ምክር አገልግሎት አንዲሁም ጊዜያዊ መጠለያ አገልግሎት እንደሚሰጥ የሁሉም አገልግሎቶች የየራሳቸው አገልግሎት መስጫ ክፍል በአንድ ቦታ ውስጥ ሲኖራቸው አገልግሎቱ የሚሰጠው በማዐከሉ በሚገኙ ፖሊሶች፣የፌደራል አቃቢያነ ህግ፣የስነ-ልቦና ምክር ባለሙያ እና በህክምና ባለሙያዎች ሲሆን አገልግሎቱ በሳምንት ለሰባት ቀናት በቀን ለ24 ሰዓት መሆኑን ገልፀውልናል፡፡

በመሆኑም ማዕከሉ ከተቋቋመ ጀምሮ ከመላው የሀገራችን ክፍል አገልግሎት ለማግኘት የሚመጡ ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳድር አቃቂ ካሊቲና የኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ተገልጋዮች አብዛኛውን ድርሻ ይወስዳሉ፡፡ ለዚህም እንደምክንያት የተገለፀው በአካባቢው የፋብሪካዎች በብዛት መኖርና የክፍለ ሀገር ሰዎች መብዛት እንደሆነ ገልፀውልናል፡፡ አገልግሎቱን መስጠት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ 2009ዓ.ም 3838 ከ14 ዓመት በታች ህፃናት1905 ከ15 አመት በታች ሴቶች ወሲባዊ ጥቃት ደርሶባቸው ለአገልግሎት ወደማዕከሉ እንደመጡ ጭምር መረጃ ሰጥተውናል፡፡

## የሀገራት አባሎች

- ወንድ አውቃለሁ ይበል እንጂ የበለጠ የምታውቀው ሴት ነች፡፡ (ህንዳውያን)
- መጨነቅ ያለብህ በድመቷ ጥቁር ወይም ነጭ መሆን ሳይሆን አይጥ መያዝ በመቻሏ ነው፡፡ (ቻይናውያን)
- ፅጌሬዳዋን የፈለገ እሾኳንም ማከበር አለበት፡፡(ፐርሻውያን)
- ከአንበሳ ጋር የምትራመድ አህያ ለፈረስ ሰላምታ አትሰጥም፡፡( ኬንያውያን)
- ፈጠራ እንደ ገል እሳት ነች እፍ ሲሏት ትፍማለች፡፡ (እንግሊዛውያን)
- ዶሮ ባይጮህም መንጋቱ አይቀርም፡፤( ሴራሊዮናውያን)
- ባለግሮሰሪው ጠጪውን ይወዳል፡፡አማቹ ሊያደርገው ግን አይፈልግም፡፡ (ጣሊያናውያን)

ምንጭ፡- ሮያል መጽሄት



## ተንከባካቢ፣ ተገልጋይን አክባሪና ርህሩህነት የተሞላበት  የጤና አገልግሎት ለእናቶች

በሃገራችንና መሰል የኢኪኖሚና ማህበራዊ እድገት ባላቸው ሃገራት የተሰሩ በርካታ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሴቶች ለወሊድና ሌሎች የእናቶችና ሕፃናት ጤና አገልግሎቶች ወደ ጤና ተቋማት በሚመጡበት ጊዜ አክብሮት የጎደለው እና ፍላጎቶቻቸውን ያላማከለ አገልግሎት እንደሚሰጣቸው አልፎ ተርፎም በደል ይደርስባቸዋል፡፡  ይህ ጉዳይ እናቶች በጤና ባለሙያዎችና ጤና ተቋማት ላይ ያላቸውን አመኔታ ከመሸርሸር ባሻገር በጤና ተቋማት የሚሰጠውን የእናቶች ጤና ክብካቤ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ከሚያደርጉ ዋነኛ ምክንያቶች መሃል ተጠቃሽ ነው፡፡ ስለሆነም ይህንን እናቶች ወደ ጤና ተቋማት በመሄድ አገልግሎት እንዳያገኙ የሚያደርግ ዋነኛ ምክንያት ለማስወገድ በጤናው ዘርፍ የትራንስፎርሜሽን እቅድ ላይ ትኩረት የተሰጠበትን -የ CRC አጀንዳ *ተንከባካቢ፣ ተገልጋይን አክባሪና ርህሩህነት የተሞላበት  የጤና አገልግሎት ለእናቶች*” እንዲሰጥ ለማስቻል ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

**ተንከባካቢ፣ ተገልጋይን አክባሪና ርህሩህነት የተሞላበት የጤና አገልግሎት ማለት ምን ማለት ነው?**

ይህ ፅንሰ-ሀሳብ ተገልጋይን ያማከለ የጤና አገልግሎት፣ የስነ-ምግባር መርሆችን ማለትም የእናቶች ነፃነት፣ ክብር፣ ስሜት፣ ምርጫዎችና ሰብዓዊ መብትን የሚያከብር፤ እንዲሁም የእናትየዋን ፍላጎት ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ለእናቶች እና ጨቅላ ህፃናት የጤና አገልግሎት መስጠትን ያጠቃልላል፡፡

**ተንከባካቢ፣ ተገልጋይን አክባሪና ርህሩህነት የተሞላበት የጤና አገልግሎት ምን ያካትታል?**

- የእናቶችን ነፃነት፣ ክብር፣ ስሜት፣እና ምርጫ ማክበር
- ተገልጋይን ያማከለ የጤና አገልግሎት መስጠት
- ሰብአዊ መብትን ማክበር እና
- የእናትየዋንና የጨቅላ ህፃኑን ፍላጎት ያማከለ አገልግሎት መስጠትን ያጠቃልላል፡፡

**በተንከባካቢ፣ ተገልጋይን አክባሪና ርህሩህነት የተሞላበት የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት አገልግሎት ሰጭዎች ማወቅ የሚገባቸው ጠቃሚ ነጥቦች፡**


- ተንከባካቢ፣ ተገልጋይን አክባሪና ርህሩህነት_የተሞላበት አገልግሎት ማግኘት የሁሉም እናቶች መብት መሆኑን፤
- ተንከባካቢ፣ ተገልጋይን አክባሪና ርህሩህነት_የተሞላበት አገልግሎት መስጠት የሁሉም ባለሙያ ሙያዊ ግዴታ መሆኑን፤
- ለእናቶች ተንከባካቢ፣ ተገልጋይን አክባሪና ርህሩህነት_የተሞላበት አገልግሎት መስጠት የእናቶችን ሞት ለመቀነስ ጉልህ ሚና እንደሚጫወት፤

ስለሆነም ሁሉም የጤና አገልግሎት ሰጭ ባለሙያዎች ተንከባካቢ፣ ተገልጋይን አክባሪና ርህሩህነት የተሞላበት  የጤና አገልግሎት በመስጠት ለእናቶች የላቀ ተጠቃሚነት የበኩላቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

## የሴት ልጅ ግርዛትና ጤና

የሴት ልጅ ግርዛት መጠን አንደ ሀገር በከተማና በገጠር የተለያየ ሲሆን እንደ EDHS 2016 መረጃ በከተማ 54 % እና በገጠር ደግሞ 68% እንዲሁም በጎሳ ደግሞ በአፋርና በኢትዮ-ሶማሌ የግርዛት መጠኑ 98 ና 99 % እንደቅደምተከተላቸው ሲሆኑ በመቀጠል ወላይታና ሀዲያ ደግሞ 92 % በማስመዝገብ  በከፍተኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡ በሀይማኖት ደረጃ ሲታይ ደግሞ 54% በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ሲሆኑ 82% ድግሞ ሲታይ የሙስሊም እምነት ተከታዮች የደርጊቱ ፈፃሚ መሆናቸውን ያሳያል፡፡

### የሴት ልጅ ግርዛት በክልል ደረጃ ሲታይ




እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን በብሔር፣ በክልልና በሀይማኖት የተቀመጡ የሴት ልጅ ግርዛት መጠን ሊያባብሱ ካስቻሉ ዋና ዋና ምክንያቶች ውስጥ ጉዳቱና የሚያስከትለው የጤና እክል ላይ የማህበረሰቡ ግንዛቤ  ውስንነት መኖሩ ዋነኛው ነው፡፡በሴቶች ላይ የጤና ችግር በማስከተል ተፅኖ የሚስከትሉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶ ላይ ግንዛቤ  በመፍጠርና ንቅናቄ በማድረግ ዋና ዋና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በመለየት የሚያስከትሉትንም የጤና ችግር በመፈተሽ ለመቀነስና ለማስቀረት በሴክተሩ የተለያዩ ስልቶችን በመንደፍ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ እንዚህን ችግሮችና የሚያስከትሉትን የጤና ችግር በተለይ ሴቶች በወሊድ ወቅት የሚደርስባቸው ስቃይ እንዲሁም ህልፈተ ሞት፣ለፊስቱላ መጋለጥ.....ወዘተ የመሳሰሉት የሴት ልጅ ግርዛት የሚያስከተለው ተፅኖዎች ናቸው፡፡

እነዚህን በሴቶች ላይ አሉታዊ ተፅኖ የሚያስከትሉትን ለመቀነስና ለማጥፋት በሚኒስቴር መስርያ ቤቱ በርካታ ስራዎች በመሰራት ላይ ይገኛሉ ከነዚህም መካከል ለጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች እና ለጤና ባለሞያዎች በተዘጋጀው የስልጠና ማንዋል ፣በአፍላ ወጣቶች ጤና ስትራቴጂ እንዲሁም በቤተሰብ ጤና ካርድ ላይ በማካተት የሚያስከትሉትን የጤና ችግር  ለማስቀረት በየደረጃው ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የግንዛቤና ንቅናቄ ስራዎች በመሰራት ግንዛቤ በመፍጠር የህብረተሰቡን አመለካከት በመቀየር በ2025 እ.ኤ.አ የሴት ልጅ ግርዛት ለማጥፋት የተያዘውን ግብ ማሳካት በጤናው ዘርፍ የተወሰዱ የመፍተሔ እርምጃዎቸን ናቸው፡፡

## የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ መዋቀሮች የስድስት ወር ዕቅድ ግምገማ ተካሄደ


በኢ.ፌ.ድ.ሪ ጤናጥበቃ ሚኒስቴር ሴቶችና ወጣቶች ጉዳይዳይ ሬክቶሬት የክልል ጤና ቢሮ፣የፌደራል ኤጀንሲዎችና ሆስፒታሎች የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ መዋቅር ባለሞያዎችና ኃላፊዎች በተገኙበት በ2009 ዓ.ም የ6ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ግምግማዊ ስልጠና በአዳማ ከተማ የባሆ ቴል ተካሄደ፡፡ በተጨማሪም ለተሳታፊዎች በራስ መተማምን እና የቡድን ግንባት በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የሪፍሬሽመንት ስልጠና ተሰጠ፡፡



## የሴት ልጅ ግርዛትን ለመከላከልና ተገቢውን የሕክምና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የምክክር መድረክ ተካሄደ

በዚሁ የምክክር መድረክ ላይ የሴት ልጅ ግርዛት ከባድ የሆነ አካላዊና ሥነ ልቦናዊ የጤና ቀውስ ከማስከተሉም ሌላ የፌስቱላ ጉዳት እንዲሁም በወር አበባ፣ በእርግዝናም ሆነ በወሊድ ጊዜ ለሞት የሚያደርስ ከፍተኛ የጤና ችግር፤ ከዚያም ባለፈ ለኤች.አይ.ቪና ተያያዥ ለሆኑ የጤና እክሎች የሚዳርግ ድርጊት መሆኑ ተገጽዋል፡፡





ወ/ሮ ያምሮት አንዷዓለም በጤና ጥበቃ ሚኒስትር የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በምክክር መደረኩ ላይ እንዳስታወቁት ሀገራችን 23.8 ሚሊዮን ሴቶችና ልጃገረዶች ግርዛት እንደተፈጸመባቸው መረጃዎች የሚያሳዩ መሆኑንና ይህም ሀገሪቱን ከፍተኛ የችግሩ ተጠቂዎች ቁጥር ከተመዘገበባቸው ሀገሮች ውስጥ አንዷ እንድትሆን አድርጓታል ብለዋል፡፡ ይህንንም ሁኔታ ለመለወጥ በሀገራችን የሴት ልጅ ግርዛትን በቀጣዮቹ ዘጠኝ (9) ዓመታት ሙሉ በሙሉ ለማስወገድ እየተሰራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

በዚሁ የምክክር መድረክ ላይ ከተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ ክልል ጤና ቢሮዎች፣ ከአጋር አካላት እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ተሳታፊዎች ተካፋይ ሆነዋል፡፡

## በጤናው ዘርፍ የአካል ጉዳተኝነት ማካተቻ ማንዋል ተዘጋጀ

የፌ/ዴ/ራ/ል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ከተለያዩ አጋረ አካላት ጋር በመተባበር በጤናው ዘርፍ የአካል ጉዳተኝነት ማካተቻ ማንዋል የመጀመሪያውን ረቂቅ አዘጋጅቶ ያጠናቀቀና የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረክም በማዘጋጀት በተለያዩ አካላት ማንዋሉን በማስተቸት አስተያየት ማሰባሰብ የተቻለ ሲሆን በፕሮግራሞ ወቅት እንደተገለፀው የማንዋሉ ዋና ዓላማ፡-




በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሁሉም ዳይሬክቶሬቶች እንዲሁም በመላው ሀገሪቱ በጤናው ዘርፍ አካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም ዜጋ የሚፈልጉትን የጤና አገልግሎት አካታችና ተደራሽ በማድረግ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የትኩረት አቅጣጫና አጀንዳዎችን ማገዝ፣ ሲሆን ዝርዝር ዓላማውም፡-

- የጤና ባለሙያዎች ስለአካል ጉዳት አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ የሚሰጡትን አገልግሎት ርህራሄ፣ ተንከባካቢ ተገልጋይን አክባሪነት የተሞላበት እንዲሆን ማስቻል፤
- የተለያየ የአካል ጉዳት ያለባቸው ተገልጋዮች ወደ ጤና ተቋም በመሄድ እንደ አካል ጉዳት አይነታቸው አገልግሎት እንዲያገኙ ማስቻል፤
- የጤና አገልግሎት ጥራት፤ ፍትሐዊነትና ተደራሽነትን በማጎልበት የአካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚነት ያረጋገጠ ስርዓት መፍጠር፤
- የጤናና ጤና ነክ መረጃዎችን ለአካል ጉዳተኞች እንደየፍላጎታቸውና የአካል ጉዳት አይነታቸው ተደራሽ እንዲሆኑ ማስቻል


መሆኑን ተገልፅዋል፡፡

## የ16ቱ ቀናትን ፀረ ፆታዊ ጥቃት ዘመቻ ቀን በልዩ ልዩ ፕሮግራሞች ተከበረ

የ2009ዓ.ም የ16ቱ ቀናትን ፀረ ፆታዊ ጥቃት ዘመቻ በአለም አቀፍ ደረጃ ለ25ኛ ጊዜ በሀገራችን ደግሞ ለ11ኛ ጊዜ ተከበረ፡፡ አከባበሩም በሀገር ደረጃ "በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ የሀይል ጥቃቶችን በመከላከልና በማስቆም የእድገትና የህዳሴ ለውጥ ዘላቂነት እናረጋግጥ!" በሚል መሪ ቃል የተከበረ ሲሆን በሴክተራችን ደግሞ "በሴቶች፣ በወጣቶችና አካል ጉዳተኞች ላይ የሚፈጸሙ የሀይል ጥቃቶችን በመከላከልና በማስቆም በጤናው ዘርፍ የተያዘውን የትራንስፎርሜሽን እቅድ እናሳካ!" በሚል መሪ ቃል ተከብሯል፡፡



የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር ከበደ ወርቁ በቦታው ተገኝተው ባደረጉት ንግግር የሀገራችን ህገ መንግስት ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችን የህግ አካል በማድረግ በአንቀጽ 35 ለሴቶች የእኩልነት መብት ዋስትና የሰጠ ሲሆን ሴቶችን ለጥቃት የሚያጋልጡ ልማዳዊ ድርጊቶች ተፈጻሚ እንደማይሆኑ፣ መንግሥትም ሴቶችን ለጥቃት ከሚያጋልጡ ልማዳዊ ድርጊቶች የመጠበቅ ግዴታ እንዳለበት ይገልጻል ብለዋል፡፡ሴክተራችንም በህገመንግስቱ ለሴቶችም ሆነ ለወንዶች የተጠበቁለት የአካል ደኅንነት፣ በሕይወት የመኖር፣ የነፃነት፣ የእኩልነት ወዘተ መብቶች መሰረት በማድረግ በሁለተኛው የጤናው ዘርፍ የትራንስፎርሜሽን እቅድ ውስጥ አንድ የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ በማድረግ የጤና አገልግሎት ፍትሃዊነትን በዋነኛነት በመያዝ አቅዶ እየሰራ ይገኛል፡፡ ለዚህም በያዝነው አመትም ጾታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ወገኖች (በሁለቱም ፆታዎች) እንደ ሀገር የተቀናጀ አገልግሎትን ለመስጠት ያስችል ዘንድ ወሲባዊ ጥቃትን የመከላከልና ምላሽ የመስጠት የአተገባበር ሰነድ በማዘጋጀት በዘርፉ ለተጎጂዎች ምላሽ ሰጪነትን የሚያጠናክር ስራ መስራቱ አንዱ ማሳያ መሆኑን ዶ/ር ከበደ ገልፀዋል፡፡



የሴቶችና ወጣቶች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወ/ሮ ያምሮት አንዱአለም በበኩላቸው ባደረጉት ንግግር በየጊዜው በጉዳዩ ዙሪያ በስፋት እየተሰራ ቢሆንም አሁንም ሴቶች ለተለያዩ ጥቃቶች ሰለባ እየሆኑ ይታያሉ፡፡ በሴቶች ላይ ከሚደርሱ ጥቃቶች ውስጥ አስገድዶ መደፈር፣ ግድያ፣ ጠለፋ፣ ያለ ዕድሜ ጋብቻ፣ ወሲባዊ ትንኮሳ፣ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ ግርዛት፣ የወሲብ መሣሪያ መሆን፣ ለአገልጋይነት መጋበዝ፣ ድብደባ፣ ወዘተ ዋነኞቹ መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡ ለእነዚህ ጥቃቶች መነሻ ምክንያቶች የተለያዩ ሲሆኑ የሴቶች በኢኮኖሚ ራስን አለመቻል፣ ባህላዊ አመለካከቶች፣ የወንዶች የበላይነት የገዘፈበት የአኗኗር ሥርዓት መኖር፣ ጥቃትን ያለማሳወቅ ባህል፣ የሥርዓተ ፆታ ግንዛቤ ማነስ ይገኙበታል ብለዋል፡፡

ይህም በሴቶች ላይ ሕይወትን የማጣት፣ የአካል ጤና ችግር፣ የሥነ ልቦና ችግር፣ ማኅበራዊ ቀውስ፣ በኢኮኖሚ ራስን ያለመቻል፣ በራስ ያለመተማመን፣ ወዘተ ያደርሳል፡፡ የጤ/ጥበቃ ሚኒስቴርም በተቀናጀ አግባብ ጥቃቶቹን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ሰነድ በማዘጋጀት ወደ ትግበራ እየተገባ መሆኑን ወ/ሮ ያምሮት ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም በዝግጅቱ ላይ በወንድ ልጆች ላይ የሚደርስ ወሲባዊ ጥቃት ጥናታዊ ጽሁፍ፣ ፆታዊ ጥቃትን የመከላከልና መላሽ የመስጠት የአተገባበር ሰነድ እንዲሁም ፆታዊ ጥቃትና ሴት አካል ጉዳተኞችን የተመለከቱ ጽሁፎች ቀርበው ከተሳታፊዎች ጋር ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡

## የአሰልጠኞች ስልጠና እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጠ

በቅዱስ ጴጥሮስ ቲቢ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል አዲስ ተመድበው ተቋሙን ለተቀላቀሉ የጤና ባለሙያዎችና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የስርዓተ ፆታ፣ አካል ጉዳተኝነትና ፆታዊ ጥቃት ላይ መሰረት ያደረገ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጠ፡፡ ስልጠናውን የቅ/ጴጥሮስ ሆስፒታል የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ያዘጋጀውና በፌ/ጤ/ጥ/ሚኒስትር የሴቶች ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ቴክኒካል እገዛ የተደረገ ሲሆን ሰልጣኞች በነበራቸው ጊዜ ደሰተኞች እንደነበሩና ስልጠናው በርካታ ቁም ነገሮች እንዳስተማራቸው ጠቅሰው እንዲዚህ አይነት ግንዛቤ ማግኘታቸው ለወደፊት ለስራቸው በእጅጉ እንደሚያግዛቸውና ለወደፊትም ቀጣይነት ያለው ስልጠና እየተዘጋጀ ለሌሎች ባለሙያዎች መሰጠት እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡



በተመሳሳይም የስርዓተ ፆታ የአሰልጣኞች ስልጠና ከደቡብ ክልል የተለያዩ ዞኖች ለተውጣጡ የጤናው ዘርፍ የስርዓተ ፆታ ተወካዮችና ባለሙያዎች ተሰጠ፡፡ የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስትር የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ባዘጋጀውና ለተከታታይ ስድስት ቃናት በተሰጠው ስልጠና ላይ የተሳተፉት ባለሙያዎች እንደገለጹት ስልጠናው በጤናው ዘርፍ የስርዓተ ፆታን ጉዳይ አካቶ ለመስራት ጉልበትና ኃይል ፈጥሮላቸው በትጋት እንዲሰሩ የሚረዳቸው መሆኑን ጠቅሰው መሰል ስልጠና ለሌሎች ስልጠናውን ላላገኙ ባለሙያዎች መሰጠት የሚቻልበትን መንግድ እንዲመቻች ጠይቀዋል፡፡

## ካነበብነዉ

### ሴቶች በአመት ከወንዶች በበለጠ 39 ቀናትን በስራ ላይ እንደሚያሳልፉ ተገለጸ



የአለም የኢኮኖሚ ፎረም ሴቶች በአመት ከወንዶች በበለጠ 39 ቀናትን በስራ ላይ እንደሚያሳልፉ ተገልጿል፡፡ይህ ደግሞ በቀን ሴቶች ከወንዶች በ50 ደቂቃ በበለጠ ጊዜ ስራ ላይ እንዲያሳልፉ እንደሚያደርጋቸው በአለም አቀፍ ደረጃ ከጾታ አንጻር ያሉ ጫናዎችንና ልዩነቶችን በዳሰሰው መረጃ ላይ ጠቅሷል።

አለም አቀፍ መረጃዎችን ተንተርሶ የቀረበው ሪፖርት እንደሚያሳየውም በጾታ ልዩነት ያለውን ጫና ለማስወገድና በሁሉ ዘርፍ ሴቶችን እኩል ከወንዶች የሚያስተናግድ ስርዓት ለመዘርጋት 170 አመታትን ይወስዳል። እንደ መረጃው በኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ደረጃ ሴቶች ከወንዶች ጋር ያላቸው ልዩነት ከፈረንጆቹ 2008 ወዲህ በከፍተኛ ደረጃ ሰፍቷል።

ከዚህ አንጻርም ወንዶች ከሴቶች በ34 በመቶ በተሻለ ገቢ በሚያስገኝላቸው ስራ ሲሰማሩ ሴቶች ግን በአብዛኛው ክፍያ በማያስገኝላቸው ስራ ላይ ጊዜያቸውን ያሳልፋሉም ነው የሚለው ሪፖርቱ። ወንዶች ገቢ በሚያስገኙ እና ተጠቃሚ በሚያደርጋቸው ስራዎች ሲሰሩ በተቃራኒው የቤት ውስጥ ስራዎች፣ ህጻናትና አረጋውያንን መንከባከብ ደግሞ የሴቶች ሚና ነው ተብሏል።ይህ ጫና እና ሃላፊነት ደግሞ እንደ ህንድ፣ ፖርቹጋል እና ኢስቶኒያ ባሉ ሃገራት ከፍ እንደሚልም ነው ሪፖርቱ የሚያሳየው።

ይሁን እንጂ እነዚህ የሴቶችን ጫና እና ያነሰ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ያጎሉ የተባሉት የቤት ውስጥ ሃላፊነቶች በርካታ ጠቀሜታዎች እንዳሏቸው የኢኮኖሚ ጠበብቶች ይናገራሉ። ይህም ከሚያስገኘው የመንፈስ እርካታና የሃላፊነት መንፈስ ባሻገር በኢኮኖሚ እንደሚመነዘር የአለም ንግድ ድርጅት ይገልጻል።እንደ ድርጅቱ መረጃ ከሆነ እነዚህ የቤት ወስጥ ሃላፊነቶች ከአንድ ሃገር አጠቃላይ የሃገር ውስጥ ምርት እድገት ውስጥ 2 በመቶውን ይሸፍናሉ። ይህ ደግሞ በብዙ ማህበራዊ ሃላፊነት ያለ ክፍያ የሚያሳልፉት ሴቶች ለሃገራቸው ኢኮኖሚያዊ እድገት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ማሳያም ነው ተብሏል።በምስራቅ አውሮፓና እና የሰሜን አውሮፓ ሃገራት (በተለምዶ ስካንዲኒቪያን ወይም ኖርዲክ ተብለው በሚጠሩት) የቤት ውስጥ ማህበራዊ ሃላፊነት በእኩል እና በክፍያ የሚከወን ነው።በእነዚህ ሃገራት ሃላፊነቱን ከመጋራት እና ካለው ክፍያ አንጻር ሴቶች በተቋማት በመቀጠር የሚያደርጉት ተሳትፎ አናሳ መሆኑ ይነገራል፡፡ አዲስ አበባ ፣ ጥቅምት 17 ፣ 2009 (ኤፍ ቢ ሲ)

## ግለ ታሪክ

### የበርካታ ሙያዎች ባለቤት የሆነችው አካል ጉዳተኛ





ስትወለድ ጀምሮ ሁለት እጅ ሳይኖራት የተወለደችውና እጅ ማጣት ከምንም ያልገደባትና ሁለት እግሮቿን በመጠቀም በርካታ ተግባራትን የምታከናውነው የ32 ዓመቷ ጄሲ ካኮክስ በልጅነት ዕድሜዋ አርቴፊሻል እጆችን ትጠቀም የነበረች ቢሆንም አርቴፊሻል እጆችዋን በመተው የቀን ተቀን ስራዎን በሁለቱም እግሮቿ ማከናወን ይመቻታል፡፡

እንደ ጄስ ካኮክስ አገላለጽ ማንኛውም ሰው ሰራሽ አካልና የአካል ድጋፍ፤ ስጋና አጥንት የተዋሀደውን እግሮችዋን እንደማይተኩላት ትናገራለች፡፡

ጄሲ ካኮክስን ከሌሎች መሰሎቿ ለየት የሚያደርጋት ባለብዙ ሙያ ባለቤት መሆኗ ነው፡፡ አካልጉዳተኝነቷና ሴትነቷ ሳያዳግታት በጽናት ችግሮችን በመጋፈጥ በርካታ ሙያዎችን አዳብራለች ከእነዚህም መካከል፡- ጄሲካ ኮክስ ከእለት እለት ስራዎችን (ከመብላተ፣ ከመጠጣት፣ ከመልበስ፣ ከመፃፍ፣... ወዘተ) በእግሮቿ ከምታከናወናቸው ተግባራት በተጨማሪ ከአምስት ዓመት በፊት ባገኘችው ፍቃድ መሰረት የመጀመሪያዋ ፍቃድ ያላት ሴት አካል ጉዳተኛ የአውሮፕላን አብራሪ ስትሆን እሷን ከሌሎች አብራሪዎች ለየት የሚያደርጋት ለእጅ የሚከብደውን ሙያ እሷ በእግሯ ማብረር በመቻሏ እ.ኤ.አ በ2008 በዓለም ድንቃ ድንቅ መዝገብ ላይ መመዝገብ ችላለች፡፡






ከዚህም በተጨማሪ በቴኳንዶ እስፖርት ጎበዝ የሆነችና በአሜሪካ ቴክዋንዶ ማህበር በኩል የጥቁር ቀበቶ የተሸለመችው የመጀመሪያዋ እንስት አካል ጉዳኛ ናት፡፡ በተጨማሪም ጆሮ ገብ የሆን ጥዑመ ዜማዎችዋን በእግሮቿ ጣቶች በመጠቀምና ከ30 ዓመቱ የቴከዋንዶ መምህሯ የነበርውና በወቅቱ አካል ጉዳተኝነቷ ከመፈቃቀር ያልገደበው ባለቤቷ ጋራ በመሆን የፒያኖ ጨዋታዎችን ማንቆርቆርም ተክናበታለች፡፡

ከዛም አልፎ ጄሲካ ምንም ማሻሻያ ያልተደረገባቸውን መኪናዎችን በእግሮቿ ከማሽከርከሯ በተጨማሪ የኮምፒተር ኪቦርድን ያላንዳች እንከን መጠቀም እንደምትችል፣

ጥልቅ ውቅያኖሶችን እስከ ወለላቸው ድርስ በመድረስ መዋኘትና በላያቸውም ላይ መንሸራሸር እንዲሁም አካል ጉዳተኝነቷ ምንም ከማድረግ እንደማያዳግታት እያሳየችና እያረጋገጠች በመሄድ ላይ የምትገኝ ወጣት ሴት ናት፡፡ ምንጭ፡- http://www.dailymail.co.uk/news/article-3143119/Arizona-Woman-Jessica-Cox-born-without-arms-learnt-fly-feet.html

### እናት እና አባቷ በመርዝ እና በገመድ ታንቃ እንድትሞት ወስነውባት የነበረችዋ ወጣት በማዕረግ ተመረቀች

ስናፍቅሽ ጌታሁን ትባላለች ወደ እዚች ምድር ከተቀላቀለች ጀምሮ ይችን አለም በአይኖቿ ለማየት አልታደለችም፡፡የአይኖቿ ብሌኖችም የእዚችን ምድር ቀለማት እና ምንነት ለማየት ያልታደሉ ሆነውባት ተፈጠረች፡፡የአይኖቿ አለማየት ወላጆቿ የአብራካቸውን ክፋይ እንዲጠሏት አደረጋት፡፡ ስናፍቅሽ አይኖቿ ማየት ባለመቻላቸው ምክንያት ብቻ ወላጆቿ ያፍሩባት ጀመር ወላጅ አባቷ መርዝ ጠጥታ ትሞት ዘንድ የፈረዱባት ሲሆን የ9ወር ቤቷ እናቷ ደግሞ "በገመድ ታንቀሽ ሙቺ እና ታንቃ ሞትችብኝ ልበል"በማለት የሞትን ፍርድ 9ወር በማህፀናቸው ተሸክመው ከእዚያም "እ" ብለው አምጠው በወለዷት እንዲሁም ጡታቸውን አጥብተው ባሳደጓት አንድያ ልጃቸው ለይ የሞት ፍርድን ፈረዱባት፡፡ ዳሩ ግን ምን ያደርጋል የስናፍቅሽ የሞት ውሳኔ በእግዚያብሄር እንጂ በቤተሰቦቿ መወሰን አልቻለም፡፡፡፡ ህይወቷን የባሰ መሪር እንዲሆን ያደረገው እናትም አባትም ሆኖ እህቴ እያለ ሲንከባከባት እና ሲያስተምራት የነበረውን ወንድሟን በሞት መነጠቋ ነው፡፡ ስናፍቅ ሀዘኗ እጅግ በረታ ቤተሰቦቿን ለመራቅም ወሰነች እና የተወለደችበትን ቀዬ ለቃ አዲስ አበባ መጣች፡፡ አዲስ አበባ አይደለም ማየት ለተሳነው ሙሉ አካል ላለውም ትከብዳለች፡፡ስናፍቅሽ አዲስ አበባም በእንቅርት ለይ ጆሮ ደግፍ ሆነችባት እና ብዙ መከራዎችን እና ፈተናዎችን እንድታሳልፍ ያለመሪ እና ያለጠቋሚ አውላላ ሜዳ ለይ ጣለቻት፡፡ስናፍቅሽ ለመጠለያነት የመረጠችው ቦታ ብቸኛ አማራጯ የቤተክርስቲያን ደጅ ሆነ፡፡ከቤተክርስቲያን አጥር ስር ሆና መዋል እና ማደርን ተጋፈጠችው፡፡ ለነፍሴ ያለ ያበላታል፡፡በእዚህ ሁኔታ እያለች በደካማ ጎኗ ገብተው የሴትነት ክብሯን ለመግፈፍ ብዙ ወንዶች አንዣበውባታል፡፡እንቅልፍም ነስተዋታል፡፡እንደውም ይባስ ብሎ ቤተክርስቲያንን ሊጠብቁ የተቀጠሩ ዘበኛም አብረሽኝ ካላደርሽ እዚህ ቦታ አታድሪም እያሉ ሁሉ አንገራግረዋታል፡፡በደረቀ ሌሊትም አላስተኛት ሲሉ ግራው የገባት ስናፍቅ ከተኛችበት ተነስታ እግሯ ወደመራት መጓዝ ጀመረች፡፡ በእዚያ ውድቅት ሌሊት ጭፈራ ቤት ሲጠጡ ያመሹ እና ሰክረው የጠነበዙ 4 ወንዶች አገኟት፡፡ እናም በስካር መንፈስ ተነሳስተው መሀል አስፓልት ላይ ሊደፍሯት ታግለው ጣሏት፡፡ በእዚህ ወቅት ምንም የማታውቀዋ ስናፍቅሽ ለፈጣሪያዋ ብቻ አንተው ታደገኝ የሚል ቃል ተናገረች፡፡ እግዜር ሳይደግስ አይጣላም እንዲሉ ወዲያው የላዳ ሹፌር መጣና ስናፍቅሽን ከመከራ ታደጋትና ወደ ታክሲው በማስገባትም ወደ ቤቱ በመውሰድ ካሳደራት በኋላ በማግስቱም 500 ብር ሰጥቶ ሸኛት፡፡ ስናፍቅሽ የወጣትነት ውበቷን ጎዳና ላይ እያደረገች ባለችበት ወቅት የመቄዶንያ በጎ ፈቃደኞች ወደ ድርጅቱ በመውሰድ እንክብካቤ አደረጉላት፡፡ ከወራቶች በኋላም መቄዶንያ ያቋረጠችውን ትምህርት እንድትማር አደረገ፡፡ በዘንድሮው አመትም በአልፋ ዩኒቨርስቲ ተምራ ከ950 ተማሪዎች 1ኛ በመውጣት በማኔጅመንት በማዕረግ ለመመረቅ በቃች፡፡ ስናፍቅሽ ወደፊት ዘማሪ እንደምትሆንም ፍላጎት አላት! ይህን ላደረገላት ለፈጣሪዋና ለመቄዶንያ የአረጋዊያን ማዕከልም ምስጋናዋን አቅርባለች፡፡

ምንጭ፡- ዋልተንጉስ ዘሸገር DireTube.com September 9, 2016




## ቃለመጠይቅ

### "የጤና ኤክስቴንሽን መርሃ-ግብሩ ሴቶችን ተጠቃሚ በማድረግ ረገድ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት!"

የጤና ኤክስቴንሽን መርሃ-ግብር በሃገራችን መሰረታዊ የጤና አገልግሎት ለሁሉም ዜጎች እንዲዳረስ ለማስቻል ከተቀረፁና ስራ ላይ ከዋሉ የጤናው ዘርፍ ስልቶች አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ ይህ መርሃ-ግብር መከላከልን መሰረት ያደረገ፣ ማህበረሰቡን ያሳተፈና ዘላቂነት ያለው የጤና አገልግሎትና መረጃ አሰጣጥን በማስፈን በርካታ ውጤቶችን አስገኝቷል፡፡



በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የጤና ኤክስቴንሽንና መሰረታዊ ጤና አግልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

ዶ/ር ዙፋን አበራ

የሀገራችንም ስም በአለም መድረኮች በበጎ እንዲነሱ ካደረጉ ዋነኛ ጉዳዮች አንዱ ሊሆንም በቅቷል፡፡ በጤና ኤክስቴንሽን መርሃ-ግብሩ እየተመዘገቡ ካሉ በርካታ ውጤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

- የእናቶችና ህፃናት ሞት በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ
- የተላላፊ በሽታዎች ክስተት መቀነስ
- የግልና የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ ባህል መዳበር
- በጤናው ዘርፍ የማህበረሰብ ተሳትፎ መጎልበት የሚሉት ተጠቃሾች ናቸዉ፡፡

በተለይም ደግሞ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚችል መልኩ ሴቶች መሆናቸው ከእናቶችና ከልጃገረዶች ጋር በቅርበት ለመስራት ጥሩ እድል ፈጥሮላቸዋል፡፡ መርሃግብሩ በዋነኝነት የሚተገበረው የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ከ50 በመቶ በላይ ጊዜያቸውን ወደ ማህበረሰቡ እና ቤት ለቤት በመሄድ እንደመሆኑ መጠን ይህ እናቶችን ወይም ሴቶችን የማግኘትና የማስተማር፣ የመመካከርና የመደገፍ እድል ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት እናቶች በቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት አስፈላጊነትና ምርጫዎች፣ በህፃናት አመጋገብና አስተዳደግ፣በቅድመ ወሊድና ድህረ ወሊድ ክትትሎች አስፈላጊነትና በወሊድ ቅድመ ዝግጅትና በጤና ተቋም ስለመውለድ አስፈላጊነት እና በመሳሰሉ ወሳኝ የጤና ጉዳዮች ዙሪያ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ ተችሏል፡፡ እናቶችም ሰሚ ብቻ ሳይሆኑ ያላቸውን ተሞክሮ፣ ስጋት፣ ፍርሃትና ማወቅ የሚፈልጉትን ጉዳይ ከጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ጋር በግልፅ አንስተው እንዲነጋገሩና እንዲወያዩ እድል ፈጥሮላቸዋል፡፡

በተጨማሪም የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ሴቶች መሆናቸው ከሴቶች የልማት ቡድኖች ጋር በቅርበት እንዲሰሩና ቡድኖቹን እንዲያጠናክሩ ትልቅ እድል ፍጥሮላቸዋል፡፡ ከዚህም በላይ እነዚህ ከ38 ሺ በላይ የሚሆኑ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ሌላውን ከማስተማር ባሻገር የሚያስተምሩትንና የሚሉትን ሆነው በመገኘት ለሌሎች ምሳሌ ሆነዋል፡፡ በዚህም በርካታ እናቶችን ወደ ጤና አገልግሎት መሳብ ችለዋል፡፡

ከዚህም ባሻገር የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ሴቶች የመሆናቸው ጉዳይ ከጤናው ዘርፍ ያለፈ ውጤት አሳይቷል፡፡ ይህም ማህበረሰቡ ሴቶች ተምረው ሌሎችን ማገልገል እንደሚችሉ ከእነኝህ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ግንዛቤ በመውሰድ ሴት ልጆቹን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልክ እንዲሁም ትምህርታቸዉን ሳያቋርጡ እንዲከታተሉ ለሚደረገዉ ጥረት አስተዋፆ እያደረገ ነዉ፡፡ በዚህም የተነሳ በየ አካባቢያቸው ያለ እድሜ ጋብቻና መሰል በሴቶች ልጆች ላይ የሚደረግ መድሎና ጥቃትን መቀነስ ተችሏል ፡፡

ይህንን ሁሉ ለውጥና ውጤት ያመጡ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችን አቅም ከዚህ በበለጠ መገንባትና ማጎልበት እንደሚገባ የሚኒስቴር መ/ቤቱ እምነት ነው፡፡ በዚህም የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችን አቅም ለማሳደግና በስልጠና ለመደገፍ በየ ሁለት አመቱ የተቀናጀ የተሀድሶ ስልጠና ይሰጣል፡ ከዚህም ባሻገር የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችን ከደረጃ 3 ወደ ደረጃ 4 ከፍ እንዲሉ የሚያስችል የስልጠና መርሃግብር ተነድፎ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችን ወደ ደረጃ 4 ከፍ ማለታቸዉ የሁለተኛው ትውልድ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ተግባራዊ ለማድረግ አንድ መስፈርት ነዉ፡፡

በተጨማሪም በጊዜ ሂደት የእነኝህ ባለሙያዎች የእድገት መሰላል ከዚህም በላይ እንዲያድግ ሁኔታዎችን አቅም በፈቀደ መልኩ ለማመቻቸት ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ ይህም ለህብረተሰቡ የሚሰጠዉን የጤና አገልግሎት ፍትሀዊነት እና ጥራት እንዲሻሻል ያስችላል፡ባለሙያዎቹን ያበረታታል፤ እንዲሁም ሌሎች ሴቶችንም ያነሳሳል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ እስከ ጤናው ሴክተር ትራንስፎርሜሽን ዘመን መጨረሻ ድረስ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና ኤጀንሲ ጋር በመተባበር 3 ሚሊዮን የሴቶች የጤና ልማት ሰራዊት መሪዎችን በደረጃ አንድ የሙያ ደረጃ ለማሰልጠን እና ለማብቃት እቅድ ተይዞ እየተሰራ ይገኛል፤ ይህም ሴቶችን በጤናው ዘርፍ በማብቃት ተሳታፊነትና ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡

## የእናቶችን ሞት ለመቀነስ አሁንም ብዙ መሰራት አለበት... ብዙ የታቀዱ ስራዎችም አሉ!



አቶ ስንታየሁ አበበ
በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የእናቶችና ሕፃናት ጤና ዳይሬክቶሬት፣
የእናቶችና ወጣቶች ጤና ቡድን አስተባባሪ

የእናቶችና ሕፃናት ጤና ዳይሬክቶሬት ከስሙ ለመረዳት እንደሚቻለው የእናቶችንና ሕፃናትን ጤና ለማሻሻል የተቋቋመ ዳይሬክቶሬት ሲሆን ይህንንም ለማሳካት በርካታ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡ እነኝህ በዳይሬክቶሬቱ የሚሰሩ ስራዎች በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ ከሴቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ጋር ጥብቅ ቁርኝት አላቸው፡፡

የእናቶችና ህፃናት ጤና ዳይሬክቶሬት ሴቶች በቤተሰብ እቅድ ዙሪያ መረጃና አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ ልጆቻቸውን አራርቀው እንዲወልዱና ያልታቀደ እርግዝናን በመከላከል የራሳቸውንና የልጆቻቸውን ጤና እንዲጠብቁ ለማድረግ በርካታ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡ የማህበረሰቡን ግንዛቤ ከማሳደግና አገልግሎቱን ከማቅረብ ጎን ለጎን የአገልግሎት ሰጪ ባለሙያዎችን አቅም በስልጠናና መሰል መንገዶች በመገንባት የሚሰጠው አገልግሎት ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን ይሠራል፡፡በተጨማሪም ሴቶች የመረጡትን የእርግዝና መከላከያ ዘዴ በአቅራቢያቸው ማግኘት እንዲችሉ ለጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የረጅም ጊዜ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎትን ጨምሮ በተያያዥ ጉዳዮች ላይ ስልጠና እየተሰጠ ነው፡፡

የነፍሰ ጡር እናቶች ቅድመ ወሊድ ክትትልን በወቅቱ(ከ4 ወር በፊት) በማስጀመርና ቢያንስ አራት ተከታታይ የእርግዝና ክትትል እንዲያደርጉ፣ እንዲሁም ወሊድ በጤና ተቋማት ብቻ እንዲደረግ በማበረታታት የእናቶችን ሞት ለመቀነስ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በዚህም ረገድ የጤና ተቋማት ምቹና የሚሰጠውም አገልግሎት ጥራቱን የጠበቀና የተገልጋይ ሴቶችን ፍላጎት ማዕከል ያደረገ እንዲሆን ለማድረግ ስራዎች እየተሰሩ ነው፡፡ በተጨማሪም ማህበረሰቡ የሴቶችን የጤና አገልግሎት ተጠቃሚነት እንዲያበረታታና እንዲደግፍ የተለያዩ የማህበረሰብ ንቅናቄዎችን በመፍጠር ዘርፈ ብዙ ስራዎች እየተተገበሩ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አሁንም ገና ብዙ መሰራት ያለበቸው ስራዎች አሉ፡፡

ከዚህ ሌላ እናቶች ጤና ተቋም ከደረሱ በኋላ የሚሰጣቸው አገልግሎት ርህራሄ፣ አክብሮትና እንክብካቤ የተሞላበት እንዲሆን የባለሙያዎችን አቅም ለማሳደግ ከሚሰጡ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችና ድጋፎች ባሻገር ማህበረሰቡም ይህንኑ እንዲረዳና እንዲገነዘብ ለማስቻል በርካታ የማህበረሰብ ንቅናቄ ስራዎች ተጀምረዋል፡፡ በተለይም በየ አመቱ የሚከበረውን ጤናማ እናትነት ወር ምክንያት በማድረግ፣ ባያዝነው አመት "ርህራሄና አክብሮት የተሞላበት የጤና አገልግሎት ለጤናማ እናትነት " በሚል መሪ ቃል በኦሮሚያ ክልል አዳማ ከተማ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር ተከብሯል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የጤናማ እናትነት ወር ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ጋር በማክበር በ"ተንከባካቢ፣ ተገልጋይን አክባሪና ርህሩህነት_የተሞላበት" የእናቶች ጤና አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ግንዛቤን የሚፈጥሩ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ ከዚህም በላይ እንደ ኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ያሉ የብዙሃን መገናኛ ድርጅቶች በጉዳዩ ዙሪያ የህበረተሰቡን ግንዛቤ የሚያሳድጉ ስራዎች ላይ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ለማስቻልም እየተሰራ ይገኛል፡፡

ሌላውና በእናቶችና ሕፃናት ጤና ዳይሬክቶሬት ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፈ ብዙ ስራዎች አንዱ የእናቶች ሞት ቅኝትና ተገቢ ምላሽ መስጠት ነው፡፡ ይህ ስራ በ2005ዓ/ም የተጀመረ ሲሆን አላማውም የእናቶችን ሞት ምክንያቶች በወቅቱና በየደረጃው በመለየትና ምላሽ በመስጠት በተለዩት ምክንያቶች የሚከሰተውን የእናቶች ሞት ማስቀረት ነው፡፡ እስከ ዛሬ ከተለያዩ አካባቢዎች በተሰበሰበው መረጃ በመንተራስ የተሰራው ትንተና የሚያሳየው ለእናቶች ሞት ምክንያት የሚሆኑት ዋና ዋና ምክንያቶች ተለይተው ምላሽ እየተሰጠባቸው ነው፡፡ ዋነኛውና ቀዋተኛው የእናቶች ሞት ምክንያት የደም መፍሰስስ ሲሆን ቀዋተኛ ያልሆነው የእናቶች ሞት ምክንያት ደግሞ የደም ማነስ ነው፡፡

በዚህ ትንተና መነሻነት ምላሽ የመስጠት ስራዎች በየደረጃው እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ ከደም መፍሰስ ጋር ተያይዞ የሚከሰተውን የእናቶች ሞት ለመቀነስ እናቶች በጤና ተቋም እንዲውልዱና የእናቶች ማቆያ ቤት በየጤና ጣቢያዎቹ እንዲኖር እየተደረገ ነው፡፡ በተጨማሪም የደም መፍሰስን መከላከልና ማከም ላይ የባለሞያዎችን አቅም ለመገንባት እየተሰራ ነው፡፡ ከስልጠናዎቹ በተጨማሪም ህብረተሰቡ ደም የመለገስ ባህል እንዲኖረውና በየአካባቢው ያሉ የደም ባንኮች ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል የሚሰሩ ስራዎች እንደተጠበቁ ሆነው የደም ባንክ በሌለባቸው አካባቢዎች በሚገኙ ሆስፒታሎች ውስጥ መለስተኛ የደም ባንክ ለማቋቋም የግብዓት ግዢ ለማድረግ የሚያስችል ልየታ ተካሂዷል፡፡ ከዚህም በላይ በየጤና ተቋማቱ የተቋቋሙ የእናቶች ሞት ቅኝትና ተገቢ ምላሽ የመስጠት ኮሚቴዎች ለእናቶች ሞት ምክንያት የሚሆኑትን ጉዳዮች በመለየት የእርምት እርምጃ በመውሰድ ላይ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል በደም ማነስ ምክንያት የሚከሰተውን የእናቶች ሞት ለመከላከል በቅድመ ወሊድ ክትትል አገልግሎት ወቅት እናቶች በእርግዝና ወቅት ሊኖራቸው የሚገባውን የአመጋገብ ስርዓት አውቀው እንዲገነዘቡ በማስቻልና እንዲሁም ለነፍሰ ጡር ሴቶች የብረት ንጥረ-ነገር(አይረን ፎሌት) በመስጠት ችግሩን ለመከላከል የሚቻልበት ስራ በመተግበር ላይ ነው፡፡

ከዚህም በላይ የሴቶችን ጤና ለማሻሻል በወሊድ ጊዜ የሚከሰተውን የፌስቱላ ህመም ልየታ በማድረግ ተጎጂዎች የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ከማህፀን መውጣት ችግር ጋር ተያይዞ ነፃ ህክምና በተመረጡ ሆስፒታሎች እየተሰጠ ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ስራዎች የሴቶችን በተለይ የእናቶችን ጤና ሁኔታ ለማሻሻል በመተግበር ላይ ያሉ ሲሆን የወጣቶችን የጤና ሁኔታም ለማሻሻል ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛሉ፡፡

እንደሚታወቀው እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በጤናው ዘርፍ ትኩረት የተሰጠው የወጣቶች ጉዳይ የስነ ተዋልዶ ጤና ብቻ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የወጣቶች ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ጉዳይ በጤናው ሴክተር ትራንስፎርሜሽን እቅድ ውስጥ ትኩረት ካገኙ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ መሆኑን ተከትሎ ከስነ ተዋልዶ ጤና ባሻገር ሌሎችንም ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች እየተካተቱ ነው፡፡ በዚህም መነሻነት አዲስ የወጣቶች ጤና እስትራቴጂ ተቀርጿል፡፡

በተጨማሪም ሌሎች በወጣት ማህበራት የሚመሩ መርሃ-ግብሮች ተቀርፀው ወጣቶች የጤና አገልግሎና መረጃ እንዲያገኙ ለማስቻል ወደ ተግባር እየተገባ ነው፡፡ ከዚህም በላይ በትምህርት ቤት ውስጥ ያሉ ወጣቶችን ለመድረስ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባባር በትምህርት ቤት የጤና መርሃ-ግብር ለመተግበር ዝግጅት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡ ይህ መርሃ-ግብር በያዝነው አመት ለናሙና በተመረጡ ውስን ት/ቤቶች የሚተገበር ሲሆን በቀጣይ በሁሉም ት/ቤቶች ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ ይህም በየት/ቤቱ የጤና ማዕከላት እንዲኖሩና ወጣቶች መረጃና አገልግሎት በማግኘት ራሳቸውን ከጤና ችግሮች እንዲከላከሉና ጤናቸውን እንዲያጎለብቱ እድል ይሰጣቸዋል፡፡ በተለይም ሴት ተማሪዎች የዚህ መርሃ-ግብር ዋነኛ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ፡፡

በአጠቃላይ የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት በማሳደግ የእናቶችን ሞት ለመቀነስ አሁንም ብዙ መሰራት አለበት! ምንም እንኳን እስከ አሁን የተገኙ ውጤቶች አበረታች ቢሆኑም በቀጣይ መሰራት የሚገባቸው በርካታ ስራዎች እንዳሉ ግልፅ ነው፡፡ ለዚህም በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ብዙ የታቀዱ ስራዎች አሉ፡፡ ለእነኝህ እቅዶች ተፈፃሚነት ሁላችንም የበኩላችንን እንወጣ፡፡

## በጤናው ዘርፍ ሴቶችን ወደ ውሳኔ ሰጭነት ሚና ለማምጣት ብዙ መሰራት አለበት!



ዶክተር ጌታቸው ቶሌራ
የሰው ሃብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

እንደሚታወቀው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በርካታ ሴት ሰራተኞች ያሉት ተቋም ነው፡፡ ነገር ግን እንደ አጠቃላይ ያሉት ሴት ሰራተኞች ቁጥር ከፍተኛ ቢሆንም በአመራርና ውሳኔ ሰጭነት ሚና ላይ ያላቸው ተሳትፎ ውስን ነው፡፡ ይህንኑ ከግምት በማስገባት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሴቶችን ወደ አመራርና ውሳኔ ሰጭነት ሚና ለማምጣት እቅዶ በመንቀሳቀስ ላይ ነው፡፡ ይህ ጥረት እንደ ሃገር የተቀመጡ አቅጣጫዎችን ጨምሮ ለጤናው ዘርፍ የተመረጡ የማትጊያና አቅም ግንባታ ስራዎችን ያጠቃልላል፡፡ ለአብነት በሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚተዳደሩ የጤና ኮሌጆችና ተቋማት ምደባና ድልድል በሚካሄድበት ጊዜ፣ በቅጥርና በእድገት፣ በስራ ላይ ምደባና በትምህርትና ስልጠና መስኮች ሴቶች እድል እንዲያገኙና ተጠቃሚ እንዲሆኑ በርካታ ስራዎች ይሰራሉ፡፡ ሴቶች መንግስት ያስቀመጠውን የአዎንታዊ ድጋፍ እርምጃ ተጠቃሚ በመሆን በትምህርትና ስልጠና አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ እገዛና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ በዚህም እድል ተጠቃሚ የሚሆኑ ሴቶች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ በማደግ ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬ ጋር በመቀናጀት ሴት ሰራተኞችን በስልጠናና መሰል የአቅም ግንባታ ስራዎች ለማብቃት ጥረቶች እየተደረገ ነው፡፡

በሌላ በኩል ሴቶች ያሉባቸውን ተደራራቢ ሃላፊነቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት የስራ ቦታን ምቹ ለማድረግ ጥረቶች ተጀምረዋል፡፡ በተለይም ሴቶች ከወለዱ በኋላ ልጆቻቸውን በበቂ ሁኔታ መንከባከብና ጡት ማጥባት እንዲችሉ ለማገዝ በመ/ቤቱ የህጻናት ማቆያ ለመስራት ከከፍተኛ አመራሩ ጋር በመነጋገር ላይ እንገኛለን፡፡ ይህም ሴቶች ልጆቻቸውን ይዘው ወደ ስራ ቦታ በመምጣት እንዲንከባከቧቸው እድል ይሰጣል፡፡ በዚህም ምክንያት ትኩረታቸውን ወደ ስራቸው ስለሚያደርጉ በስራቸው ውጤታማ ይሆናሉ፡፡

ሴት ሰራተኞችን የማብቃት ስራ የሰው ሃብት ልማት ወይም የሴቶችና ወጣቶች ዳይሬክቶሬቶች ጉዳይ ብቻ መሆን የለበትም፡፡ ምንም እንኳን እነኝህ የስራ ክፍሎች ትልቁን ድርሻ ቢወስዱም ሁሉም ባለ ድርሻ አካላት በቅንጅትና በጋራ አቅደው ሊሰሩት የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሁሉም ዳይሬክቶሬቶች የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬትን በማማከር በአመታዊ እቅዳቸው ውስጥ በማካተትና በመተግበር በየ ደረጃው ያሉ ሴት ሰራተኞችን ማብቃት ይጠበቅብናል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በጤናው ዘርፍ የተሰማሩ አገልግሎት ሰጭ ባለሙያዎች የሚሰጡት አገልግሎት ርህራሄ፣ አክብሮትና እንክብካቤ የተሞላበት እንዲሆን ለማስቻል ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር እየተሰራ ይገኛል፡፡ ይህም የእናቶችን ተጠቃሚነት በማሳደግ ሊከሰት የሚችለውን ሞት በመቀነስ ሃገሪትን በጤናው ዘርፍ ያስቀመጠቻቸውን እቅዶች ለማሳካት ያግዛል፡፡



በጤናዉ ዘርፍ የሴቶችና ወጣቶች መዋቅሮች ስድስተኛዉ አመታዊ የምክክር መድረክ ታሳታፊዎች በከፊል
አሶሳ ሰኔ 2008



በጤናዉ ዘርፍ የሴቶችና ወጣቶች መዋቅሮች ስድስተኛዉ
አመታዊ የምክክር መድረክ ታሳታፊዎች በሕዳሴዉ ግድብ
ጉብኝት ላይ
አሶሳ ሰኔ 2008



በጤናዉ ዘርፍ የሴቶችና ወጣቶች መዋቅሮች ስድስተኛዉ አመታዊ የምክክር መድረክ ታሳታፊዎች በከፊል
አሶሳ ሰኔ 2008



በጤናዉ ዘርፍ የሴቶችና ወጣቶች መዋቅሮች ስድስተኛዉ
አመታዊ የምክክር መድረክ የላቀ አፈፃፀም ላሳዩ መዋቅሮች
እዉቅና ሲሰጥ
አሶሳ ሰኔ 2008




በሚኒስቴር መስርያቤቱ፣ በክልሎችና በተጠሪ ተቋማት የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ መዋቅሮች
የ2009 ዓ.ም እቅድ በጋራ ሲያቅዱ



በጤናዉ ዘርፍ የሴቶችና ወጣቶች መዋቅሮች አምስተኛዉ አመታዊ የምክክር መድረክ
ታሳታፊዎች በከፊል

ባህርዳር ሰኔ 2008


Women
Empowerment
Leadership




# HAPPY WOMEN'S DAY